# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# የመንግስት ተሽከርካሪዎች አጠባበቅ፣አጠቃቀም እና አወጋገድን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

የካቲት 2003 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

# አርዕስት ማውጫ

**ክፍል አንድ ........ 2**

*መግቢያ* ........ 2

*የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ አመሠራረት* ........ *2*

*የኤጀንሲው ዓላማ* ........ *3*

*የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር* ........ *3*

*የኤጀንሲው ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል* ........ *5*

*የኤጀንሲው የፋይናንስ ምንጭ* ........ *5*

የኦዲቱ ዓላማ ........ 5

የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ ........ 6

የኦዲቱ አካባቢ (AUDIT AREA) ........ 6

የኦዲቱ የተኩረት አቅጣጫዎች (AUDIT ISSUES) ........ 6

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት ........ 7

የአሠራር ሂደት መግለጫ (PROCESS DESCRIPTION) ........ 7

*የመንግሥት ተሸከርካሪ ስምሪት የአሰራር ሂደት* ........ *8*

*የመንግሥት ተሸከርካሪ የነዳጅ አጠቃቀም የአሰራር ሂደት* ........ *8*

*የመንግሥት ተሸከርካሪ የጥገና የአሠራር ሂደት* ........ *8*

*የመንግስት ተሸከርካሪ አወጋገድ የአሠራር ሂደት* ........ *9*

**ክፍል ሁለት ........ 10**

የኦዲት ግኝቶች ........ 10

*የመንግሥት ተሸከርካሪዎች አስተዳደር መመሪያን በተመለከተ፤* ........ *10*

*የመንግሥት ተሸከርካሪዎች ዝርዝር መረጃ አያያዝን በተመለከተ፡* ........ *13*

የተሸከርካሪዎች ባለቤትነትን ማረጋገጥ፣ ስምሪት፣ ጥገና እና ተያያዥ ሁኔታዎችን የሚገልጹ መረጃዎችን በተመለከተ ........ 13

የተሸከርካሪዎች ርክክብ መረጃዎችን በተመለከተ ........ 15

ተሸከርካሪዎች ላይ አደጋ ሲደርስ የሚያዙ መረጃዎችን በተመለከተ፤ ........ 15

*የመንግስት ተሸከርካሪዎች አጠቃላይ ሁኔታን የሚገልጽ ልዩ ሪፖርት ማቅረብን በተመለከተ* ........ *17*

*ተሸከርካሪዎች አጠቃቀም እና አጠባበቅን በተመለከተ* ........ *18*

ተሸከርካሪዎች በአንድ ሊትር ነዳጅ መጓዝ የሚችሉትን እርቀት ማጥናት እና መረጃ መያዝን በተመለከተ ........ 18

ተሸከርካሪን የመጠበቅ ኃላፊነትን በተመለከተ፤ ........ 21

የተሸከርካሪ ነዳጅና ቅባት አጠቃቀምን በተመለከተ፤ ........ 26

የመንግስት ተሸከርካሪዎች የመድን ዋስትናን በተመለከተ፤ ........ 27

የተሸከርካሪዎች የእሳት አደጋ ማጥፍያ መሣሪያን በተመለከተ፤ ........ 28

በመንግሥት ተሸከርካሪዎች ጎን በሮች ላይ የመ/ቤታቸው ዓርማ መለጠፍን በተመለከተ፤ ........ 29

*የመንግስት ተሸከርካሪዎች ጥገናን በተመለከተ* ........ *30*

የውጭ ጋራዥ የመምረጫ መስፈርትን በተመለከተ ........ 30

የጥገና ጥያቄ የሚቀርብላቸው ተሸከርካሪዎች የደረሰባቸው ብልሽት እና የሚያስፈልጋቸው ጥገና በገለልተኛ አካል የሚረጋገጥ መሆኑን በተመለከተ፡ ........ 32

ተሸከርካሪዎች ለጥገና ጋራዥ ሲገቡ ጥገናው የሚወስደው ጊዜ መወሰንን በተመለከተ ........ 33

የተሸከርካሪዎች አቀማመጥን በተመለከተ፤ ........ 35

*የመንግስት ተሸከርካሪዎች አወጋገድን በተመለከተ* ........ *36*

ተሸከርካሪዎች ማገልገል ያለባቸውን ዘመን በተመለከተ ........ 36

የተሸከርካሪ አስወጋጅ ኮሚቴ መሰየምን በተመለከተ፤ ........ 38

የሚወገዱ ተሸከርካሪዎችን ዝርዝር እና ያሉበትን ሁኔታ የሚገልጽ መረጃን በተመለከተ ........ 39

ሊወገዱ የሚገባቸው ተሸከርካሪዎች በወቅቱ መወገዳቸውን በተመለከተ ........ 40

የተወገዱ ተሸከርካሪዎች በመመሪያው መሠረት የተወገዱ መሆኑን በተመለከተ ........ 43

ተሸከርካሪዎችን በማስወገድ የተገኘ ገቢ ለማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ መደረጉን በተመለከተ ........ 46

የተወገዱ ተሽከርካሪዎችን ከመዝገብ መሰረዝን በተመለከተ ........ 46
*የመንግስት ተሽከርካሪዎችን ለማስተዳደር ተገቢው የሰው ኃይል የተመደበ መሆኑን በተመለከተ*.47

**ክፍል ሦስት ........ 49**

*መደምደሚያ* ........ 49

**ክፍል አራት ........ 51**

*የማሻሻያ ሀሳቦች* ........ 51

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. ግዙፋዊ ህልውና ያለው የተናጠል ዋጋው ብር ሁለት መቶ እና በላይ የሆነ እንዲሁም ከአንድ ዓመት በላይ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚኖረው እና አገልገሎት በመስጠት ላይ ያለ ንብረት በሙሉ በመንግስት ቋሚ ንብረትነት የሚመደብ ሲሆን፣ ከዚህ ውጭ ያለው በአላቂ ንብረትነት ውስጥ ይካተታል፡፡ የመንግሥት ተሽከርካሪ በቋሚ ንብረት ውስጥ የሚመደብ ሲሆን፣ ከሌሎች ቋሚ ንብረቶች አንፃር ሲታይ ለመግዛትም ሆነ ለመጠቀም ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ እና ለብክነት የተጋለጠ መሆኑን ከተለያዩ አካላት የሚወጡ መረጃዎች ይገልፃሉ፡፡ በመሆኑም ለመንግስት ተሽከርካሪ ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶ በአግባቡ ሊጠበቅና ሊያዝ ይገባል፡፡

### የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ አመሠራረት

2. የመንግስት ተሽከርካሪዎችን በቅርብ የማስተዳደር ኃላፊነት ያለባቸው ንብረቱን የተረከቡት እና የሚጠቀሙበት መ/ቤቶች ቢሆኑም በገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥር የመንግሥት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር መምሪያ የመንግስት ተሽከርካሪዎችን አስተዳደር በመንግሥት የንብረት አስተዳደር ተግባር ውስጥ በማካተት  እስከ ሰኔ 1997 ዓ.ም ድረስ ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ ከሐምሌ 1997 ዓ.ም ወዲህ የመንግሥት ግዥ ኤጀንሲ በአዋጅ ቁጥር 430/97 ለገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተጠሪ ሆኖ እራሱን ችሎ ሲቋቋም የመንግስት የግዥ ተግባራትን እንዲያከናውን ተደርጓል፡፡

3. በገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ህዳር 2001 ዓ.ም ከተጠናው መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት (BPR) በኃላ የመንግሥት ንብረት አስተዳደር ተግባር በመንግሥት ግዥ ኤጀንሲ ቢከናወን የተሻለ መሆኑ ስለታመነበት ኤጀንሲው በአዋጅ ቁጥር 649/2001 የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በሚል በአዲስ መልክ እንዲቋቋም የተደረገ ሲሆን፣

የመንግስት ተሽከርካሪዎች አስተዳደር በዚሁ ኤጀንሲ በኩል እንደማንኛውም የመንግስት ቋሚ ንብረት እንዲከናወን ተደርጓል፡፡

## የኤጀንሲው ዓላማ

4. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ አስፈጻሚ አከላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 649/2001 መሠረት የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጄንሲ የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት፡-

- ፍትሃዊ በውድድር ላይ የተመሠረተ ግልጽ እና አድልዎ የሌለበት ለመንግሥት ገንዘብ ተመጣጣኙ ዋጋ ማስገኘት የሚያስችል የግዥ አፈጻጸምና ዘመናዊ የመንግሥት ንብረት አስተዳደር መኖሩን ማረጋገጥ፤
- የመንግስት መ/ቤቶች በአዋጅ የተዘረዘሩትን ጠብቀው መሥራታቸውን መከታተል፤
- በፌዴራል መንግሥት ውስጥ ያለውን የግዥ አፈጻጸም እና የንብረት አስተዳደር አቅም ማሳደግ፤
- በሀገር አቀፍ ደረጃ የተጣጣመ የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ሥርዓት እንዲኖር ማድረግ፤
- የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ሥርዓት ተቀባይነት ካላቸው ዓለም አቀፍ ሥርዓቶች ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ማድረግ፡፡

## የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር

5. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ አስፈጻሚ አከላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 649/2001 መሠረት የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጄንሲ የሚከተሉት ሥልጣን እና ተግባራት ተሰጥቶታል፡፡ እነሱም፤

- በመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ፖሊሲዎች መርሆች አፈጻጸሞች ላይ የፌዴራል መንግሥትን ማማከር፤ ለክልሎችና ለከተማ አስተዳደሮች የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፤

- በፌዴራል መንግሥት ውስጥ ያለውን የመንግሥት ግዥ አፈጻጸም እና የንብረት አስተዳደር ሥርዓት ተግባራዊነት በመከታተል ለሚኒስትሩ ሪፖርት ማድረግ እና በህግና በአፈጻጸም ሥርዓቱ ላይ የማሻሻያ ሃሳቦች ማቅረብ፤
- አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የግዥና የንብረት አስተዳደር ሥልጠና እንዲሁም የግዥና ንብረት አስተዳደር አፈጻጸምን ለመምራት የሚያስፈልገው ችሎታ፤ በሙያው ለመሠማራት ተፈላጊ የሆነው ማስረጃ ዓይነት እና የሙያው ዕድገት ሊከተል የሚገባው ሂደት መወሰኑን ማረጋገጥ፤
- መደበኛ የግዥ ሰነዶች አሠራርን የሚመሩ ቅጾች እና ሌሎች ለግዥና ንብረት አስተዳደር አግባብነት ያላቸውን ሰነዶች ማዘጋጀት፣ ሥራ ላይ እንዲውሉ እና ወቅታዊ እንዲሆኑ ማድረግ፤
- ከተፈቀዱ መደበኛ የግዥ ዘዴዎች፣ ሰነዶች፣ አሠራሩን ከሚመሩ ቅጾች እና ሌሎች ለግዥ አፈጻጸም አግባብነት ካላቸው ሰነዶች ውጪ ግዥ ለመፈጸም ወይም ከተፈቀዱ የንብረት አወጋገድ ሥርዓቶችና ስልቶች ውጭ ንብረት ለማስወገድ በመንግስት መ/ቤቶች ጥያቄ ሲቀርብለት ጥያቄውን መርምሮ ውሳኔ መስጠት፤
- በመንግስት መ/ቤቶች አገልግሎት ላይ ለሚውሉ ዋና ዋና ቋሚ ንብረቶች ደረጃ ማውጣትና አፈጻጸሙን መከታተል፤
- ከገበያ ጋር የማይጣጣም ዋጋ በሚያቀርቡ እና ሌሎችንም የዚህን አዋጅ እና በሚኒስቴሩ የሚወጣውን መመሪያ እና ድንጋጌዎች የሚቃረኑ ተግባራትን የሚፈፅሙ ዕጩ ተወዳደሪዎች፤ አቅራቢዎች ወይም በመንግሥት ንብረት ማስወገድ ሂደት ተሳታፊዎች ላይ በቀረበ አቤቱታ መነሻነት ማስጠንቀቂያ የመስጠት፤ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ በመንግስት ግዥ ወይም የንብረት ማስወገድ ሂደት እንዳይሳተፍ የማገድ፤

- በመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር አፈጻጸም ላይ በራሱ መርሐ ግብር ወይም በሚደርሰው ጥቆማ መነሻነት ኦዲት ማካሄድ ወይም እንዲካሄድ ማድረግ፤

ናቸው፡፡

## የኤጀንሲው ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል

6. የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ተጠሪነቱ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒሲቴር ሲሆን፣ አንድ ዋና ዳይሬክተር፣ አንድ ምክትል ዳይሬክተር እና ለዋና ዳይሬክተሩ ተጠሪ የሆኑ ስድስት ዳይሬክቶሬቶች አሉት፡፡ ኤጀንሲው በጠቅላላው 101 የሰው ኃይል እንዲኖረው የተፈቀደለት ቢሆንም ይህ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት በተጠናቀቀበት ወቅት ዋና ዳይሬክተሩን፣ ምክትል ዋና ዲሬክተሩን እና 6 ዳይሬክተሮችን ጨምሮ በሥራ ላይ ያለው የሰው ኃይል 70 ነው፡፡

## የኤጀንሲው የፋይናንስ ምንጭ

7. የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ሥራውን ለማከናወን ከመንግሥት በጀት የሚመደብለት ሲሆን፣ በ2001 እና በ2002 በጀት ዓመታት ለሚያከናውናቸው ተግባራት ማስፈጸሚያ በቅደም ተከተሉ መሠረት ብር 1.3 እና 1.1 ሚሊዮን መደበኛ በጀት የተመደበለት ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ በ2001 በጀት ዓመት ብር 0.8 ሚሊዮን በ2002 በጀት ዓመት በ6 ወራት ውስጥ ብር 0.37 ሚሊዮን ሥራ ላይ አውሏል፡፡

# የኦዲቱ ዓላማ

8. የመንግስት ተሽከርካሪዎች አጠቃቀም እና አወጋገድ ተግባር በኤጀንሲው እና የእነዚህ ንብረቶች ተጠቃሚ በሆኑት የመንግስት መ/ቤቶች ህግና ደንብን ተከትሎ በቁጠባ (economically) እና በብቃት (efficiently) እየተከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ ሲሆን፣ ይህንን በተመለከተ የአሠራር ችግሮች ካሉ ችግሮቹ በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦችን ማቅረብ ነው፡፡

## የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

9. ኦዲቱ የሸፈነው ከ2000 እስከ 2002 የሥራ ዘመናት ባለው ጊዜ የተሽከርካሪ አጠቃቀም እና አወጋገድን በተመለከተ የተከናወኑ ሥራዎችን ነው፡፡ ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ሲሆን፣ ስምንት የፌዴራል መ/ቤቶች በናሙና ተመርጠው ታይተዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለሠላሳ ሦስት የፌዴራል መ/ቤቶች መጠይቅ ተዘጋጅቶ በመላክ ምላሽ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡

10. በዚህም መሠረት በኤጀንሲው እና በናሙና በተመረጡ የፌዴራል መ/ቤቶች ከተሽከርካሪ አስተዳደር ጋር ተያያዥ የሆኑ እና አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች በመከለስ፣ በሥራቸው የሚያስተዳድሯቸው የመንግስት ተሽከርካሪዎች ያሉበትን ሁኔታ በአካል በማየት፤ መጠይቅ ከተላከላቸው መ/ቤቶች በተሰበሰቡ መረጃዎች ላይ ትንተና በማካሄድ እንዲሁም ለኤጀንሲው እና በናሙና ለተመረጡ መ/ቤቶች የሥራ ኃላፊዎች ቃለ መጠይቅ በማቅረብ ለዝርዝር ኦዲቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

## የኦዲቱ አካባቢ (Audit area)

11. ለዝርዝር ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አከባቢ የመንግስት ተሽከርካሪዎች አጠቃቀም እና አወጋገድ በቁጠባ እና በብቃት እየተከናወነ መሆኑን ማረጋገጥ የሚል ነው፡፡

## የኦዲቱ የተኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues)

12. ከላይ በተገለጸው የኦዲት አከባቢ ሥር ሁለት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች (Audit issues) ተቀምጠዋል፡፡ እነርሱም፡-

1. የመንግሥት ተሽከርካሪዎች አጠቃቀም በቁጠባ እና በብቃት እየተከናወነ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡

   1.1. የመንግሥት ተሽከርካሪዎችን ስምሪት በብቃት እና በቁጠባ ለመቆጣጠር እና ለመከታተል የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን ማረጋገጥ፣

1.2. የመንግሥት ተሽከርካሪዎች ጥገና በብቃት እና በቁጠባ መከናወኑን ለመቆጣጠር እና ለመከታተል የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት የተዘረጋና ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን መገምገም፣

2. የመንግሥት ተሽከርካሪዎች አወጋገድ በቁጠባ እና በብቃት እየተከናወነ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡

2.1. የመንግሥት ተሽከርካሪዎች ማገልገል የሚገባቸውን ጊዜ ያህል እያገለገሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

2.2. አገልግሎት የማይሰጡ የመንግሥት ተሽከርካሪዎችን ለማስወገድ መንግሥት ያወጣው መመሪያ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑ እና የማስወገዱ ተግባር በቁጠባ እና በብቃት እየተከናወነ መሆኑን ማረጋገጥ፣

የሚሉት ናቸው፡፡

# የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

13. በኦዲት ቡድኑ ለተመረጡት ሁለት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች 34 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች የተዘጋጁ ሲሆን፣ እነዚህን የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ለማዘጋጀት መሠረት የሆኑት የኤጀንሲው ማቋቋሚያ አዋጅ፤ የንብረት ግዥን እና አስተዳደርን የሚመለከቱ የተለያዩ መመሪያዎች፤ የኤጀንሲው ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ከ2000 እስከ 2002 ዓ.ም ያለው የኤጀንሲው ዓመታዊ ዕቅድ፣ የዕቅድ ክንውን ሪፖርቶች እና የኤጀንሲው መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት (BPR) ሰነድ ናቸው፡፡ በተዘጋጁት የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ላይ የኤጀንሲው ኃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ተደርጎ ስምምነት ላይ ተደርሶአል፡፡ መመዘኛ መስፈርቶቹ ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ1 ተያይዘዋል፡፡

# የአሠራር ሂደት መግለጫ (Process Description)

14. ይህ የተሽከርካሪ አስተዳደር የአሠራር ሂደት የተቀመጠው ጥር 1977 የወጣውን የመንግሥትና ሕዝባዊ ድርጅት ተሽከርካሪዎች ግዥ፣ ስምሪት፣ አጠቃቀም እና ጥገና መመሪያን፣ ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ተሽከርካሪዎችና

መሳሪያዎች ስለሚወገዱበት ሁኔታ የወጣ መመሪያን፣ የመንግሥት ቋሚ ንብረት አስተዳደር መመሪያን /ኅዳር ታህሳስ 2000/ እና የመንግሥት ግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እንደ ግባት /input/ በመጠቀም ነው፡፡

## የመንግሥት ተሽከርካሪ ስምሪት የአሰራር ሂደት

15. የተሽከርካሪ ጥያቄ የሚያቀርበው አካል ለክፍል ኃላፊው በተሽከርከሪ መጠየቂያ ፎርም የስምሪት ጥያቄ ያቀርባል፡፡ የክፍል ኃላፊው ፈርሞ ወደ ስምሪት ክፍል ይመራዋል፡፡ የስምሪት ክፍሉ የጥያቄውን አግባብነት አገናዝቦ የሚቆይበትን ጊዜ ግምት ውስጥ በማስገባት ተሽከርካሪው የሚነሳበትንና የሚመለስበትን ሰዓት በመወሰን ተሽከርካሪውን ይፈቅዳል፡፡ ተሽከርካሪው ሥራውን ጨርሶ ሲመለስ በተፈቀደለት ሰዓት መሠረት ስለመመለሱ ያረጋግጣል፤

## የመንግሥት ተሽከርካሪ የነዳጅ አጠቃቀም የአሰራር ሂደት

16. የመንግሥት ተሽከርካሪ ነዳጅ ሲጨርስ አሽከርካሪው በነዳጅ መጠይቅያ ቅጽ ለትራንስፖርትና ስምሪት ክፍሉ የነዳጅ ጥያቄ ያቀርባል፡፡ የትራንስፖርትና ስምሪት ክፍሉ ከጥያቄው በፊት የተቀዳውን ነዳጅ ተሽከርካሪው ከተጓዘው ኪሎ ሜትር ጌጅ ጋር ካገናዘበ በኃላ የተጠየቀውን ነዳጅ ይፈቀዳል፡፡ ነዳጁ በትክክል ስለመቀዳቱ አሽከርካሪው ለትንስፖርትና ስምሪት ክፍሉ ደረሰኝ ያቀርባል፡፡

## የመንግሥት ተሽከርካሪ የጥገና የአሠራር ሂደት

17. የመንግስት ተሽከርካሪ ሲበላሽ ሹፌሩ የጥገና መጠየቂያ ቅጽ /Request for service/መተ0016 በመሙላት የጥገና ጥያቄ ለትራንስፖርትና ስምሪት ክፍሉ ያቀርባል፡፡ የትራንስፖርትና ስምሪት ክፍሉ ወደ ተክኒክ እንስፔክሽን ክፍል ይመራዋል፡፡ የቴክኒክ እንስፔክተሩ በተሽከርካሪ ማስረከቢያ ቅጽ መሠረት ተሽከርካሪውን ከሹፌሩ በመረከብ የብልሽቱን ዓይነት አረጋግጦ በጥገና ማዘዣ ቅጽ /shop repair order or work order/ በመሙላት መ/ቤቱ የራሱ ጋራዥ ካለው ወደ ሚመለከተው ጥገና ክፍል ይመራዋል፡፡ መ/ቤቱ የራሱ ገራዥ ከሌለው የጥገና አገልገሎቱን የሚሰጡ የግል ጋራዦችን በጨረታ ኮሚቴ በማወዳደር የተሻለ የጥገና አገልገሎት ይሰጣል ተብሎ በጨረታ መመሪያ

መሠረት ጨረታውን ያሸነፈው ጋራዥ ጥገናውን እንዲያከናውን ይደረጋል፡፡ ከተጠገነም በኃላ ተሽከርካሪው በትክክል ስለመጠገኑ በቴክኒክ እንስፔክተሩ ሲረጋገጥ በመውጫ ፎርም ሹፌሩ እንዲረከብ ይደረጋል፤

## የመንግስት ተሽከርካሪ አወጋገድ የአሠራር ሂደት

18. ተሸከርካሪውን የሚያስተዳድረው ክፍል ተሽከርካሪው ጥቅም እንደማይሰጥ ከተሽከርካሪው የሕይወት ታሪክ ከሚገኙት መረጃዎች በመነሳት እና ተሽከርካሪው ያለበትን ሁኔታ በአካል በማየት በጥገና እንስፔክተር ከተረጋገጠ በኃላ የማስወገድ ጥያቄ ለንብረት አስተዳደር ይቀርባል፡፡ የንብረት አስተዳደሩም ለንብረት አስወጋጅ ኮሚቴ /Disposal committee/ ይመራዋል፡፡ የንብረት አስወጋጅ ኮሚቴው የሚወገደውን ተሽከርካሪ በተመለከተ የቀረቡለትን መረጃዎች በመመርመር ሊወገድ የሚገባው መሆኑን ሲያምንበት የማስወገጃ ቅጽ /Equipment Disposal Form/ በመሙላት ለመ/ቤቱ ኃላፊ ያቀርባል፡፡ በመ/ቤቱ ኃላፊ እንዲጸድቅ ከተደረገ በኃላ ለገማች ኮሚቴ ቀርቦ የተሽከርካሪው መሸጫ ዋጋ እንዲወጣለት ተደርጎ ተሽከርካሪው በመንግሥት ተሽከርካሪ አወጋገድ መመሪያ መሠረት እንዲወገድ ይደረጋል፤

# ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች

### የመንግሥት ተሽከርካሪዎች አስተዳደር መመሪያን በተመለከተ፤

19. የመንግሥት መ/ቤቶች በሥራቸው ያሉትን የመንግስት ተሽከርካሪዎች የሚያስተዳድሩበት መመሪያ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

20. በሀገር አቀፍ ደረጃ ጥር 1977 ዓ.ም በትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር ከ30 ዓመታት በፊት የወጣ መመሪያ ያለ ቢሆንም ሀገሪቱ አሁን ካለችበት ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ሊያሠራ የማይችል እና የማይጣጣም በመሆኑ የተመለከትናቸው የፌዴራል መ/ቤቶች እንደማይጠቀሙበት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህን ችግር ለማቃለል በሀገር አቀፍ ደረጃ ወቅታዊ ሁኔታን ባገናዘበ መልኩ እንደ መርህ የሚያገለግል የተሽከርካሪ ግዥ፤ ስምሪት፣ አጠቃቀም እና ጥገና መመሪያ አልተዘጋጀም፡፡

21. በናሙና ተመርጠው በታዩ የፌዴራል መ/ቤቶች የመንግሥት ተሽከርካሪ አስተዳደር መመሪያን በተመለከተ የሚከተሉት ሁኔታዎች ታይተዋል፤ በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፤ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፤ በውሃና ኢነርጅ ሚኒስቴር፣ በማእድን ሚኒስቴር፣ በመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን እና በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን በ1977 ዓ.ም የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር በሀገር አቀፍ ደረጃ ሥራ ላይ እንዲውል ያወጣውን የመንግሥት ተሽከርካሪ ግዥ፣ ስምሪት፣ አጠቃቀም እና ጥገና መመሪያ እየተጠቀሙበት እንዳልሆነ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

22. ስለሁኔታው የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፤ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ መመሪያው የእዝ ኢኮኖሚን መሠረት በማድረግ የወጣ ከነፃ ገበያ ኢኮኖሚ አሠራር ጋር ሊጣጣም ስላልቻለ ለመጠቀም አስቸጋሪ በመሆኑ ቅጾቹን ብቻ ሚኒስቴሩ በመጠቀም ላይ መሆኑን፤ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ተሽከርካሪን በተመለከተ ግዥና ጥገና የሚከናወነው መንግሥት በጥቅል ስለግዥ ባወጣው አዋጅና መመሪያ መሠረት መሆኑን እና ስምሪት ደግሞ ቀደም ሲል በነበረው መመሪያ መሠረት

መሆኑን፤ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ መመሪያውን መርህ ሳይለቅ መ/ቤታቸውን በሚጠቅም መልኩ በማሻሻል እየተጠቀሙበት እንደሚገኝ፤ የማእድን ሚኒስቴር ሚኒስትር በ1977 ዓ.ም የተዘጋጀው መመሪያ ረጂም ጊዜ የቆየ መሆኑን እና በአሁኑ ወቅት በሚኒስቴሩ ስምሪት ክፍል እንደማይገኝ ሆኖም የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት መሠረት በማድረግ አዲስ መመሪያ እስኪወጣ ድረስ ከቀድሞው መመሪያ ሊያሠራ የሚችለውን በመምረጥ ተግባራዊ እንደሚያደርጉ፤ የመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን የድጋፍ ሰጪ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር መመሪያው ወቅታዊ ባለመሆኑ በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ አለመደረጉን ሆኖም መመሪያው ሲሻሻል ተግባራዊ እንደሚያደርጉ ገልጸዋል፡፡

23. የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር በትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር በ1977 ዓ.ም ወጥቶ የነበረው መመሪያ መጋቢት 15 ቀን 1985 ዓ.ም ከትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር በወጣው መመሪያ የተተካ መሆኑ እና ተግባራዊ እየተደረገ እንደሚገኝ፣ የተሽከርካሪ ግዥን በተመለከተ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እ.ኤ.አ መስከረም 1992 ዓ.ም በቁጥር 0151/1/18 ባለሥልጣኑ ማንኛውም ግዥ በራሱ ማከናወን እንዲችል ውክልና እንደተሰጠው፣ ስለተሽከርካሪ ስምሪትና ቁጥጥር በባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ የተላለፈ መመሪያ በሥራ ላይ እደሚገኝ እንዲሁም ጥገናን በተመለከተ በመሣሪያዎች አስተዳደር ሥርዓት (Equipement Management System–EMS) በዝርዝር የተገለጸ መሆኑን በቀረበላቸው የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ የኦዲት ቡድኑ ሥራውን አጠናቆ ከወጣ በኋላ የገለጹ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት ከላይ የተገለጹት መረጃዎች ተጠይቀው ባለመቅረባቸው ሁኔታውን ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

24. በትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር በመጋቢት 15 ቀን 1985 ዓ.ም የወጣውን መመሪያ የኦዲት ቡድኑ ተመልክቶታል፡፡ ሆኖም ይህ መመሪያ በዚሁ ሚኒስቴር መ/ቤት በ1977 ዓ.ም የወጣውን መመሪያ የሚተካ መሆኑን በግልጽ አያሳይም፡፡

25. ስለሁኔታው የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ እስከ አሁን የመንግሥት ተሽከርካሪን በሚመለከት የተለየ መመሪያ ያልወጣ ቢሆንም የፌዴራል መንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ አዋጅ ቁጥር 649/2001 ሲወጣ በአጠቃላይ " ከአዋጁ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በአዋጁ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት እንደማይኖረው" በመገለጹ ጥር 1977 በትራንስፖርት እና መገናኛ ሚኒስቴር የወጣው መመሪያ ተለይቶ ባይጠቀስም የተሻረ መሆኑን፤ በመንግሥት ንብረት አስተዳደር ሥርዓት ውስጥ የመንግሥት ተሽከርካሪ ከቋሚ ንብረቶች ጎራ ስለሚካተት ሌሎች ቋሚ ንብረቶች በሚመዘገቡበትና በሚጠበቁበት ሁኔታ መጠበቅ እንደሚኖርበት በቀድሞው የመንግስት ንብረት መመሪያ ቁጥር 6/1991 የተገለፀ መሆኑን እና ይህ መመሪያ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲተላለፍ መደረጉን፤ አሁን በቅርቡ የመንግሥት ቋሚ ንብረት አስተዳደር ማንዋል ላይ ሥልጠና ተሰጥቶ ተግባራዊ እንዲደረግ አመራር መሰጠቱን፤ የተሽከርካሪ አወጋገድን በሚመለከት መጋቢት 10/1989 ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት የተላለፈውን መመሪያ በመከተል ሲፈጸም መቆየቱን ገልጸዋል፡፡

26. በተጨማሪም ተሽከርካሪ ልዩ ባህርያት ስላሉት የተለየ መመሪያ እንደሚያስፈልገው በኤጀንሲው በኩል የሚታመንበት ቢሆንም የመንግሥት ግዥ ኤጄንሲ የመንግሥት ግዥ ላይ ብቻ ባተኮረ ሁኔታ የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት ካገባደደ በኃላ የመንግስት ንብረት አስተዳደርንም ደርቦ እንዲያከናውን ሲደረግ በ2001 መጨረሻ የመንግሥት ግዥንና የንብረት አስተዳደርን አጣምሮ የያዘ አዲስ አዋጅ እንዲወጣ ከመደረጉ በስተቀር የንብረት አስተዳደርን በሚመለከት የተካሄደ ዝርዝር የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት ባለመካሄዱ ለመንግስት ተሽከርካሪዎች አስተዳደር የሚሆን ልዩ መመሪያ ማዘጋጀት ትኩረት ሳይሰጠው መቆየቱን ገልጸዋል፡፡

27. ሀገሪቱ ለሌሎች ተግባራት ከምታወጣው ወጪ ጋር ሲነጻጸር ለመንግስት ተሽከርካሪ ግዥ፣ ጥገና፣ የነዳጅና ቅባት፣ ወዘተ… የሚወጣው ወጪ ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዝ ቢሆንም ይህ ቀደም ብሎ ከ30 ዓመታት በፊት የተዘጋጀ

መመሪያ እንዲሻሻል አለመደረጉ ወይም ይህን መመሪያ የሚተካ እና በሀገር አቀፍ ደረጃ ተዘጋጅቶ መንግሥታዊ መ/ቤቶች በቀጥታ ሊጠቀሙበት የሚችሉት ወይም የራሳቸውን ነባራዊ ሁኔታ በማገናዘብ የራሳቸው መመሪያ ለማዘጋጀት እንደመርህ የሚያገለግል ወቅታዊ የሆነ መመሪያ አለመኖሩ የመንግሥት ተሽከርካሪዎችን አስተዳደር በቁጠባ እና በብቃት እንዳይከናወን እንዲሁም ክትትል እና ቁጥጥር ለማድረግ እንዳይቻል ያደርጋል፡፡

## የመንግሥት ተሽከርካሪዎች ዝርዝር መረጃ አያያዝን በተመለከተ፡

28. የመንግስት መ/ቤቶች በኃላፊነታቸው ሥር የሚገኙ ተሽከርካሪዎች በምን መልኩ እንደተረከቧቸው፣ የተጓዙበት ኪሎ ሜትር ብዛት፣ የተጠቀሙበትን ነዳጅ፣ ቅባት እና ለሎች ተዛማጅ ቁሳቁሶችን መጠን፣ የተደረገላቸውን ጥገና እና ተያያዥ ወጪዎችን የሚመለከቱ ዝርዝር መረጃዎች በማጠናቀር ሊይዙ ይገባል፡፡

29. በናሙና ተመርጠው በታዩ የፌዴራል መ/ቤቶት የተሽከርካሪዎች ባለቤትነትን፣ ስምሪትን፣ ጥገናን፣ ርክክብ ወዘተ… የሚገልጹ መረጃዎች በአግባቡ ተይዘው ያልተገኙ ሲሆን፣ ዝርዝር ሁኔታው እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### የተሽከርካሪዎች ባለቤትነትን ማረጋገጥ፣ ስምሪት፣ ጥገና እና ተያያዥ ሁኔታዎችን የሚገልጹ መረጃዎችን በተመለከተ

30. በናሙና ተመርጠው በታዩ የፌዴራል መ/ቤቶቸ የተሽከርካሪ ማህደሮች በናሙና ሲታዩ በተወሰኑ መ/ቤቶች ማለትም በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፣ በማዕድን ሚኒስቴር ፣ በውኃ ሀብት ሚኒስቴር ፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ በንግድና ኢዱስትሪ ሚኒስቴር እና በመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን በአብዛኛው የተሽከርካሪ ማህደሮች ውስጥ የሚያስተዳድሯቸውን ተሽከርካሪዎች በምን መልኩ እንደተረከቧቸው ማለትም በግዥ፣ በእርዳታ፣ በዝውውር ወይም በስጦታ እንደተገኙ የሚያስረዳ ግልጽ መረጃ አልተገኘም፡፡ በግብርና ሚኒስቴር እያንዳንዱን ተሽከርካሪ ሚኒስቴሩ በምን መልኩ እንደተረከበው ብቻ ሳይሆን ስምሪት፣ ጥገና እና ተያያዥ ሁኔታዎችን የሚገልጹ

መረጃዎች በተሽከርካሪዎች ፋይል ውስጥ እንዲያዙ አለመደረጉን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

31. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የድጋፍ ሥራ ሂደቶች ማስተባበሪያ ዳይሬክተር ያሉት ተሽከርካሪዎች ከ20 ዓመት በፊት የነበሩና ከሌሎች መ/ቤቶች የመጡ በመሆናቸው ስለነዚህ ተሽከርካሪዎች ሁኔታ የሚገልጽ መረጃ በአጭር ጊዜ ማግኘት አለመቻሉን፣ የማዕድን ሚኒስቴር ሚኒስትር የመ/ቤቱ ንብረት ክፍል ተሽከርካሪዎች በግዥ ሲገቡ በግዥው ማስረጃ መሠረት የገቢ ደረሰኝ የሚያዘጋጅ ቢሆንም በመረጃ መልክ በተሽከርካሪ ማህደር የማይያዝ መሆኑን ሆኖም በተሰጠው አስተያየት መሠረት ወደፊት ማስተካከያ እንደሚያደርጉ፣ የውኃ ሀብት ሚኒስቴር የአገልግሎቶች አቅርቦትና ቁጥጥር ዳይሬክተር የተሽከርካሪዎች ርክክብ የሚከናወነው የተሽከርካሪውን ግዢ ደረሰኝ፣ የመንገድ ወረቀትና ፓኪንግ ሊስት (packing list) በማመሳከር እንደሆነ እና ከላይ የተጠቀሱት ሰነዶች ከግዢ ክፍል በማስታወሻ የሚላኩለት መሆኑን፤ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ በግዥ የሚገቡ ተሽከርካሪዎች በግዥ ሰነድ መሠረት፤ በዕርዳታ የሚገቡ ተሽከርካሪዎች ደግሞ ከዕርዳታ ሰነድ ጋር ተገናዝበው ገቢ የሚደረጉ መሆኑን፤ ሆኖም በክፍያ ወቅት ከክፍያ ሰነድ ጋር በእንስፔክሽን ሪፖርት (inspection report) ውስጥ ተካቶ ስለሚያያዝ ለማግኘት እንደሚያስቸግር፤ የንግድና ኢዱስትሪ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ባለፉት አሥር ዓመታት ውስጥ መ/ቤቱ በግዥ፣ በእርዳታ እና በስጦታ ያገኘው ተሽከርካሪ አለመኖሩን እና የተወሰኑ ተሽከርካሪዎች ንግድ ሚኒስቴር እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሲዋሃዱ የተገኙ ቢሆንም መረጃቸው አብሮ አለመምጣቱን ገልጸዋል፡፡

32. የግብርና ሚኒስቴር የግዥ፣ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክተር ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ቀደም ሲል የተሽከርካሪዎች ክፍፍል ሲደረግ የተሽከርካሪዎች መረጃዎች ወደ ክልል በመበታተናቸው የተወሰኑ ተሽከርካሪዎች ላይ የመረጃ አለመሟላት እንደሚታይ፤ ሆኖም ችግሩን ለመፍታት ከመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን ጋር በመጻጻፍ ክትትል

እየተደረገ መሆኑን፣ በተጨማሪም  ተሽከርካሪ የሚገዛው በሚኒስቴሩ አማካይነት በሚተገበሩ የተለያዩ ፕሮጀክቶች በኩል ብቻ መሆኑን እና የንብረት ገቢ ደረሰኝ ተቆርጦላቸው ማስረጃው ከፕሮጀክት ፋይናንስ ሰነዶች ጋር ተያይዞ እንደሚገኝ ሆኖም ተሽከርካሪዎች ከነዚህ ፕሮጀክቶች ወደ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚዘዋወሩበት ወቅት ተሽከርካሪዎቹ  ያላቸው ታሪክና መረጃዎች አብረው ባለመምጣታቸው መረጃዎቹን ለማሟላት አለመቻሉን እና ለወደፊት ክትትል በማድረግ መረጃዎቹን የማሰባሰብ ተግባር እንደሚከናወን ገልጸዋል፡፡

## የተሽከርካሪዎች ርክክብ መረጃዎችን በተመለከተ

33. በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን፡ በንብረት አስተዳደር ዙሪያ አንድ ኃላፊ በሌላ ኃላፊ ሲተካ ተሽከርካሪዎች በትክክል ተቆጥረው አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ፣ ተበላሽተው ጥገና ላይ ያሉ፣ ሊወገዱ የተዘጋጁ፣ የጠፉ፣ ወዘተ ተብለው ተለይተው ርክክብ የማይፈፀም በመሆኑ አሁን በንብረት ኃላፊነት ቦታ የሚገኙት ሠራተኛ የተሽከርካሪዎችን ሁኔታ በሚመለከት ለቀረበላቸው ጥያቄ ግልጽ መረጃ ለመስጠት አልቻሉም፡፡

## ተሽከርካሪዎች ላይ አደጋ ሲደርስ የሚያዙ መረጃዎችን በተመለከተ፤

34. በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን በተሽከርካሪ ላይ አደጋ ሲደርስ የሚሞላው የአደጋ ሪፖርት ባለሙያዎች በቦታው በመገኘትና በጥንቃቄ የአደጋውን መንስዔ በማጣራት እና በተጨባጭ መረጃ በማስደገፍ ሳይሆን በአብዛኛው አሽከርካሪዎች የሚሰጡትን ሪፖርት ብቻ መሠረት በማድረግ እንደሚዘጋጅ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ አሽከርካሪዎች ጥፋተኛ ሆነው ሲገኙ ራሳቸውን ለማዳን በሚያደርጉት ጥረት ትክክለኛ መረጃ የማይያዝ መሆኑን እና ባለሥልጣኑም ይህን ችግር ለመፍታት አስተዳደራዊ እርምጃ ስለመውሰዱ መረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡

35. በዚሁ ባለሥልጣን በየዓመቱ በተለያዩ የሥራ ክፍሎች ማለትም ከኢንሹራንስ ዋና ክፍል፣ Claims and Technical Support section እና Safety, Traffic Signs and Making Branch ያሉ የተሽከርካሪ የአደጋ ጊዜ ሪፖርት መረጃዎች የማይጣጣሙና እርስ በርስ የሚጋጩ ናቸው፡፡ ለመጥቀስ ያህል ከትራፊክ የሚመጣ የአደጋ ሪፖርት እና በመ/ቤት የሚቀርብ የአደጋ መንስኤና ጥፋተኝነት ሪፖርቶች

የሚቃረኑ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህንንም ችግር ለመፍታት ባለሥልጣኑ የወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡

36. ስለጉዳዩ የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት ማንኛውም የመ/ቤቱ የሥራ ኃላፊ፣ አዲስ ቦታ ሲመደብ በሥሩ የሚገኙትን ንብረቶች ስለመረከቡ እንዲፈርም የማይጠበቅበት ቢሆንም በክፍሉ የሚገኙ ንብረቶች ዝርዝር መረጃ እንደሚኖረው፣ እንዲሁም በተሽከርካሪ ላይ አደጋ በሚከሰትበት ወቅት የሚዘጋጀው የአደጋ ሪፖርት መረጃዎች የማይጣጣሙና እርስ በርስ የሚጋጩ መሆናቸውን በተመለከተ በባለሥልጣኑ የተጠናው ጥናት ሰነድ ላይ የተቀመጠውን የመፍትሄ ሃሳብ ተግባራዊ ለማድረግ እንቅስቃሴ ላይ መሆኑን የገለጹ ቢሆንም ከላይ እንደተገለጸው በንብረት አስተዳደር ቦታ ላይ የተቀመጡት ኃላፊ ተሽከርካሪዎችን የሚመለከት መረጃ ሊያቀርቡ አልቻሉም፡፡

37. ይህንንም በተመለከተ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የመረጃ አያያዝ ድክመት ከአፈጻጸም ጋር የተያያዘ ችግር መሆኑን እና እስከ ቅርብ ጊዜ በሥራ ላይ በነበረው የመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 6/91 አንቀጽ 11 ላይ የመንግሥት መ/ቤቶች በትውስት ወይም በስጦታ ያገኙዋቸውን ንብረቶች መረጃ በምን መንገድ መያዝ እንዳለባቸው የተመለከተ ቢሆንም መመሪያውን ተከትለው አለመፈፀማቸው ስህተት መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በማከልም በኤጀንሲው የንብረት ኦዲት የተጀመረው በቅርቡ በመሆኑና የተሽከርካሪዎችን የህይወት ታሪክ የሚያሳይ ማህደር መ/ቤቶች መያዝ እንዳለባቸው በግልፅ የሚያመለክት ድንጋጌ ባለመኖሩ በማካሄድ ላይ በሚገኙት የንብረት ኦዲት ቼክ ሊስት (Check List) ላይ የተጠቀሰውን ተግባር በሚመለከት ክትትል ማድረግ ባይካተትም በጥናት ላይ በተመሠረተ መንገድ ለተሽከርካሪ የተለየ መመሪያ ሲወጣ እንዲካተት በማድረግ የመ/ቤቶች የተሽከርካሪ መረጃ አያያዝ ላይ በቅርብ ክትትል እንደሚደረግበት ገልጸዋል፡፡

38. ከተሰበሰቡት መረጃዎች ለመገንዘብ የተቻለው በነዚህ በናሙና በታዩት መ/ቤቶች የተሽከርካሪዎች የሕይወት ታሪክ ማለትም የባለቤትነት፣ የስምሪት፣

የጥገና፣ የርክክብ እና ሌሎች ተያያዥ መረጃዎች በአግባቡ ተጠናቅረው እንደማይያዙ፤ የተያዙትም መረጃዎች እርስ በእርስ የማይጣጣሙና የሚጣረሱበት ሁኔታ መኖሩን ነው፡፡ የእነዚህ መረጃዎች በተገቢ ሁኔታ አለመያዝ ተሽከርካሪውን በአግባቡ ለመጠበቅ፣ ለመጠቀም እና ለማስወገድ የሚከናወኑ ተግባራት በቁጠባ እና በብቃት ማከናወን እንዳይቻል ያደርጋል፡፡

## የመንግስት ተሽከርካሪዎች አጠቃላይ ሁኔታን የሚገልጽ ልዩ ሪፖርት ማቅረብን በተመለከተ

39. የመንግስት መ/ቤቶች የሚያስተዳድሯቸውን የመንግስት ተሽከርካሪዎች አጠቃላይ ሁኔታ የሚገልጽ ልዩ ሪፖርት በየዓመቱ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ማቅረብ አለባቸው፡፡

40. በናሙና ከታዩት የፌዴራል መ/ቤቶች መካከል የግብርና ሚኒስቴር የሚያስተዳድራቸውን የመንግሥት ተሽከርካሪዎች ቆጠራ የሚያከናወን ቢሆንም የተሽከርካሪዎቹን አጠቃላይ ሁኔታ የሚገልጽ ሪፖርት በየዓመቱ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚንስቴር እንደማያቀርብ፤ በመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን ደግሞ የተሽከርካሪ ቆጠራ በየዓመቱ እንደማይከናወን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የግብርና ሚንስቴር የግዥ፣ ፋይናንስ እና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክተር በመሥሪያ ቤት ደረጃ የተሽከርካሪ ቆጠራ እንደሚደረግ ሆኖም ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚንስቴር ሲጠየቅ ብቻ የአጠቃላይ የንብረት ቆጠራ የሚገልጽ መረጃ እንደሚላክ፤ የመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን የድጋፍ ሰጪ ዳይሬክተር በባለሥልጣኑ መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት ሲደረግ ሁለት ዓመት በመውሰዱና ይህን ተከትሎ በተፈጠረ የአደረጃጀት ለውጥ ምክንያት የንብረት የሥራ ሂደት በባለሥልጣኑ ተሽከርካሪዎች ላይ ዓመታዊ ቆጠራ ሊያደርግ አለመቻሉን ሆኖም በተሽከርካሪ ስምሪት፣ ጥገና እና ጠቅላላ አገልግሎት የሥራ ሂደት በኩል ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም ለገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተሽከርካሪን በተመለከተ ሪፖርት እንዳልቀረበ ገልጸዋል፡፡

41. ይህንንም በተመለከተ የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ተሽከርካሪን በተመለከተ ሪፖርት

እንዲቀርብ የሚያስገድድ የተለየ መመሪያ ባለመኖሩ መ/ቤቶች የሚያስተዳድሯቸውን ተሽከርካሪዎች ወቅታዊ ሁኔታ የሚገልጽ ሪፖርት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ማቅረብ አለማቅረባቸውን በሚመለከት ቁጥጥር አለመደረጉን ገልጸዋል፡፡

42. ከተሰበሰቡት መረጃዎች ለመገንዘብ የሚቻለው በእነዚህ መ/ቤቶች ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ልዩ ሪፖርት የማይቀርብ መሆኑን ሲሆን፣ ይህ ሁኔታ የተሽከርካሪ አስተዳደርን በተመለከተ ተጠያቂነትና ግልጽነት እንዳይኖር እና በተሽከርካሪ አስተዳደር ዙሪያ የሚታዩ ችግሮች እንዳይታወቁ እና ወቅታዊ ትኩረት እንዳይሰጣቸው ያደርጋል፡፡

# ተሽከርካሪዎች አጠቃቀም እና አጠባበቅን በተመለከተ

## ተሽከርካሪዎች በአንድ ሊትር ነዳጅ መጓዝ የሚችሉትን እርቀት ማጥናት እና መረጃ መያዝን በተመለከተ

43. የመንግሥት ተሽከርካሪዎች በዓይነትና በሞዴል ተለይተው በአንድ ሊትር ነዳጅ ስንት ኪሎ ሜትር መጓዝ እንደሚችሉ በጥናት ተረጋግጦ እንደአስፈላጊነቱ እየተጠናቀረ መረጃ ሊያዝ ይገባል፡፡

44. በናሙና ከታዩ ስምንት የፌዴራል መ/ቤቶች ውስጥ አምስቱ ከሚያስተዳድሯቸው ተሽከርካሪዎች መካከል የተወሰኑት የተጓዙትን ርቀት የሚለካ ጌጅ የሌላቸው ሲሆን፡ ጌጅ ያላቸውም ሆነ የለሌላቸው ተሽከርካሪዎች በሊትር ምን ያህል ኪሎ ሜትር መጓዝ እንደሚችሉ በየጊዜው ጥናት እየተደረገ መረጃ የሚያዝበት ሁኔታ አለመኖሩን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

45. በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ካሉት 267 ተሽከርካሪዎች መካከል ከ53 እስከ 80 የሚሆኑት፣ በግብርና ሚኒስቴር ካሉት 260 ተሽከርካሪዎች መካከል 15 ተሽከርካሪዎች፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ካሉት 81 ተሽከርካሪዎች መካከል 2፣ በማእድን ሚኒስቴር የተወሰኑ ተሽከርካሪዎች፣ በትራንስፖርት ባለስልጣን አብዛኛው በኃላፊዎች እጅ የሚገኙ ተሽከርካሪዎችና አንድ የፑል ተሽከርካሪ ጌጅ የሌላቸው መሆኑን ከቀረቡ መረጃዎች፣ ከተደረጉ ቃለ መጠይቆች እና በአካል የተሽከርካሪዎቹን ሁኔታ በማየት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

46. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ የተወሰኑ ተሸከርካሪዎች በአብዛኛው በእርጅና ምክንያት እንዲሁም ሦስት ተሽከርካሪዎች ዳሽ ቦርዳቸው በመበላሸቱ ጌጃቸው የማይሠራ መሆኑን እና የጥገና ዋጋቸው በመንግስት ለተሽከርካሪዎቹ ጥገና ከሚመደበው በጀት በላይ በመሆኑ ማስጠገን እንዳልተቻለ፤ የግብርና ሚኒስቴር የግዥ፣ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክተር ጌጃቸው የማይሠራ ተሽከርካሪዎች አሮጌ በመሆናቸው የመለዋወጫ ዕቃ ባለመገኘቱ ጥገና ማድረግ አለመቻሉን እና በከተማ ውስጥ ብቻ እንዲንቀሳቀሱ መደረጉን፤ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ሁኔታው በአገልግሎት ብዛት የሚያጋጥም መሆኑን እና ለጊዜው ጌጃቸው በገበያ ላይ ባለመገኘቱ መጠገን አለመቻሉን፤ የማእድን ሚኒስቴር ሚኒስትር የተጓዙበትን ኪ.ሜ መለኪያ ጌጅ የሌላቸውን ተሽከርካሪዎች ለመጠገን የጌጅ ግዥ ለመፈጸም ሞዴላቸው በገበያ ላይ ባለመኖሩ እና ቢገኝም የዋጋው ከፍተኛ መሆን ችግሩን ለማቃለል እንዳላስቻላቸው ሆኖም ወደፊት ችግሩን ለማስወገድ ጥረት እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡

47. የመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን ድጋፍ ሰጪ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክቴር ጌጃቸው የማይሠራ ተሽከርካሪዎች ያሉ ቢሆንም የተሽከርካሪዎቹ ሞዴል የቆየ በመሆኑ በገበያ ላይ ማግኘት እንዳልተቻለ ሆኖም በኃላፊዎች የተያዙ ተሽከርካሪዎች በየወሩ የተወሰነውን ነዳጅ ብቻ ስለሚሰጥ ችግር እንደማይገጥማቸው ገልጸዋል፡፡

48. በውኃና ኢነርጂ ሚኒስቴር፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ በግብርና ሚኒስቴር እና በንግድና ኢዱስትሪ ሚኒስቴር ተሽከርካሪዎች በአይነት እና በሞደል ተለይተው በአንድ ሊትር ነዳጅ ስንት ኪ.ሜ መጓዝ እንደሚችሉ እንደአስፈላጊነቱ በየተወሰነ ጊዜ እርቀት በጥናት የሚረጋገጥበት እና መረጃ የሚያዝበት ሁኔታ አለመኖሩ ተረጋግጧል፡፡

49. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታየተጠና ጥናት ባይኖርም በመ/ቤቱ ውስጥ ወጥ የሆነ የአሠራር መመሪያ በመኖሩ የአሮጌ መኪና ስድስት ኪ.ሜ. ለሌሎቹ

ደግሞ እንደተሽከርካሪዎቹ አገልግሎት ዘመን እንደሚለያይ፤ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ የተጠና ጥናት ባይኖርም የተደራጀ መረጃ እንዳለ እና በየጊዜውም ተሽከርካሪዎቹ በተለያየ የመንገድ አይነት ላይ እየተነዱ በሊትር የሚገዝሁት እርቀት እንደሚያዝ፤ የግብርና ሚኒስቴር ግዥ፣ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክተር በአንደኛ እና በሁለተኛ ደረጃ መንገዶች ላይ የመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች የነዳጅ አጠቃቀም ጥናት እንዳለ ሆኖም ግን ከመ/ቤቱ የሥራ ጸባይ የተነሳ ከዋናው መንገድ ውጭ ስለሚወጣ በኪ.ሜ. የነዳጅ አጠቃቀም ላይ ወጣ ገባ እንደሚኖረው፤ የንግድና ኢዱስትር ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ በጥናት የተረጋገጠ ባይሆን የተሽከርካሪውን ዕድሜና ይዞታ ያገናዘበ ግምታዊ መረጃ እንዳላቸው የገለፁ ቢሆንም መረጃው እንዲቀርብ ተጠይቆ አልቀረበም፡፡

50. ይህን ጉዳይ አስመልክቶ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ እያንዳንዱ የመንግስት መ/ቤት በሥሩ የሚገኙት የመንግስት ተሽከርካሪዎች በሊትር ምንያህል ኪ.ሜ. እንደሚጓዙ የሚያመለክት መረጃ ቢኖራቸው ለቁጥጥርና ተሽከርካሪዎቹ መወገድ አለባቸው ወይስ የለባቸውም የሚለውን ውሳኔ ከመስጠት አንጻር ጠቀሜታ እንዳለው ስለሚታመን ለተሽከርካሪ የተለየ መመሪያ በሚዘጋጅበት ጊዜ እንዲካተት እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡

51. የእነዚህ የመንግስት መ/ቤቶች በስራቸው የሚያስተዳድሯቸው የተወሰኑ ተሽከርካሪዎች የኪሎ ሜትር መቆጣጠሪያ ጌጅ አለመሥራቱ እና የሚያስተዳድሯቸው ተሽከርካሪዎች በአይነት እና በሞዴል ተለይተው በአንድ ሊትር ነዳጅ ስንት ኪ.ሜ መጓዝ እንደሚችሉ በጥናት የተረጋገጠ መረጃ አለመኖር የእነዚህን ተሽከርካሪዎች የነዳጅ ፍጆታ መጠን ከተጓዙበት እርቀት ጋር በማነፃጸር የነዳጅ ፍጆታቸው አዋጪ መሆን አለመሆኑን በማመዛዘን አዋጪ ሆኖ በማይገኝበት ወቅት ተሽከርካሪውን ማስወገድ ወይም መጠቀምን በተመለከተ አግባብነት ያለውን እርምጃ ለመውሰድ እንዳይቻል ያደርጋል፡፡

## ተሽከርካሪን የመጠበቅ ኃላፊነትን በተመለከተ፤

52. የመንግሥት ተሽከርካሪን በዋናነት የመጠበቅ ኃላፊነት ተሽከርካሪውን በኃላፊነት የተረከበው እና የሚጠቀምበት መ/ቤት መሆን አለበት፡፡

53. በናሙና ከታዩት የፌዴራል መ/ቤቶች መካከል በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ተሽከርካሪዎች በአካል አለመገኘት፣ መጥፋት፣ ከባለሥልጣኑ እውቅና ውጭ መሸጥ፣ በአሽከርካሪዎች ጥንቃቄ ጉድለት ምክንያት ተሽከርካሪዎች የመገልበጥ፣ የተሽከርካሪ አካሎች መጉደል፣ የተሽከርካሪ ሞተሮች መጥፋት እና የተሽከርካሪ ሞተሮች በወቅቱ ሳይወገዱ ጥንቃቄ በጎደለው ሁኔታ ለፀሐይ፣ ለዝናብና ለአቧራ ተጋልጠው የሚገኙ መሆኑን ከሰነዶች እና በአካል ተሽከርካሪዎቹ የሚገኙበትን ሁኔታ በማየት ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

54. የዚሁ ባለሥልጣን ሦስት የኮንስትራክሽን ተሽከትካሪዎች ያለ መ/ቤቱ እውቅና በሽሬ እንደስላሴ ከተማ ታህታይ ቆራሮ ካለክትትል እና ጥበቃ ተትተው በከተማው አስተዳደር እንዲሸጡ መደረጉን እና ባለሥልጣኑ ተሽከርካሪዎቹ ለምን ያለመ/ቤቱ ዕውቅ እና ፍቃድ በሌላ አካል እንዲሸጡ እንደተደረገ ከመጠ የቅ ፋንታ የባለሥልጣኑን የባንክ ቁጥር በመጥቀስ የተሸጠው ገንዘብ ገቢ እንዲደረግለት መጠየቁን ለማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን፣ የባለሥልጣኑ ንብረት የሆኑ አራት ተሽከርካሪዎች ስለመጥፋታቸው ሪፖርት የቀረበ ቢሆንም ባለሥልጣኑ በዚህ ጉዳይ የወሰደው አስተዳደራዊ እርምጃ ስለመኖሩ የሚያስረዳ መረጃ ተጠይቆ አልቀረበም፡፡

55. ሁለት የባለሥልጣኑ የኮንስትራክሽን ሮለሮች በተቀናጀ መልኩ የስርቆት ሙከራ እንደተደረገባቸውና ከመ/ቤቱ ቅጥር ግቢ በተሽከርካሪ ተጭነው ሊወሰዱ ሲሉ ከስርቆት የተረፉ ቢሆንም በውስጥ ኦዲት በኩል ይህ የስርቆት ሙከራ ከባለሥልጣኑ እስከማሰናበት የሚያደርስ የዲስፕሊን ግድፈት መሆኑ ተገልጾ ሪፖርት መቅረቡን፣ በአሽከርካሪዎች ተገቢው ጥንቃቄ ባለመደረጉ ምክንያት አራት ተሽከርካሪዎች የመገልበጥ አደጋ በተደጋጋሚ እንደደረሰባቸው ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ሆኖም ባለሥልጣኑ በዚህ ጉዳይ

የወሰደው የዲስፕሊንም ሆነ አስተዳደራዊ እርምጃ ስለመኖሩ የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡

56. ከዚህም በተጨማሪ በዓለም ገና ዲስትሪክት የሚገኝ የተሽከርካሪ ዕቃዎች መጋዘን ያረጀ፣ ቆርቆሮው የተገነጣጠለ እና በውስጡ የሚገኙ በርካታ የተሽከርካሪ ሞተሮችና አካሎች አንዱ በአንዱ ላይ ተደራርበው እና በአቧራ ተሸፍነው ለብክነት ተጋልጠው የተቀመጡ መሆኑን፣ በዚሁ በለሥልጣን በታህሳሥ 17/1998 ዓ.ም. ከመሣሪያዎች ማኔጅመንት ዋና ክፍል ለጎንደር ዲስትሪክት ከተጻፈ የቢሮ ማስታወሻ ላይ እንደተመለከተው ሃያ አራት (24) የመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች ሞተሮቻቸውን ጨምሮ ዋና ዋና አካሎቻቸው መጥፋታቸው የተገለጸ ቢሆንም ባለሥልጣኑ በዚህ ጉዳይ ላይ የወሰደው አስተዳደራዊ እርምጃ ስለመኖሩ የሚያስረዳ መረጃ ሊቀርብ አለመቻሉን፣ በቃሊቲ እና በዓለም ገና ዲስትሪክት በርካታ የተሽከርካሪ ሞተሮች እና ዋና ዋና አካሎች ለፀሐይ፣ ለዝናብና ለአቧራ ተጋልጠው በወቅቱ ሳይወገዱ ሳር በቅሎባቸው የሚገኙ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል ፡፡







ምስል1. በአውራ ጎዳና በአለም ገና ዲስትሪክት በቃሊቲ በርካታ የተሽከርካሪ ሞተሮችን ጨምሮ ዋና ዋና አካሎቻቸው ለአቧራ፤ ለፀሀይ እና ለዝናብ የተጋልጡ፡፡

57. ስለጉዳዩ የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት ጠፉ ከተባሉት ተሽከርካሪዎች መካከል ሁለቱ የአገልግሎት ጊዜያቸውን የጨረሱ እና የንብረት ማስወገጃ ቅፅ ተሞልቶላቸው ከሌሎች ንብረቶች ጋር መወገዳቸውን እና ተሽከርካሪዎቹ መወገዳቸው ለማረጋገጥ ለኦሮሚያ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ጥቅምት 17 ቀን 2003 ዓ.ም በቁጥር አነ2/6/13-28 ለተፃፈ ደብዳቤ መልስ እየጠበቁ እንደሚገኙ፤ ሁለት ዶዘሮች መጥፋትን በተመለከተ ሪፖርት እንደደረሳቸው አጣርቶ ውጤቱን የሚያቀርብ ኮሚቴ ተዋቅሮ፣ ለአካባቢው ፖሊስ ሪፖርት መደረጉን እና ጉዳዩ ስርቆቱ በተፈጸመበት ክልል ፀረ-ሙስና ኮሚሽን እጅ የሚገኝ መሆኑን፣ በሌላ አካል እንዲሸጡ የተደረጉ የኮንስትራክሽን ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ በባለሥልጣኑ የአዲግራት ዲስትሪክት ከፍተኛ ክትትል እንደተደረገና መስተዳድሩ በጨረታ መሸጡን እና ከዲስትሪክቱ አቅም በላይ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

58. በተጨማሪም ከአሽከርካሪዎች የጥንቃቄ ጎድለት በተሽከርካሪዎች ላይ የደረሰውን አደጋ በተመለከተ የተወሰኑት ተሽከርካሪዎች ለኢትዮጵያ መድን ድርጅት ሪፖርት ተደርጎ የድርጅቱ ኃላፊዎችም የባለሙያውን ሪፖርት እያጠኑት እንደሆነና ውሳኔው እየተጠበቀ መሆኑን፣ የተቀሩት ደግሞ የመንገድ ጥገናና ግንባታ ፕሮጀክት ኃላፊዎች ጥፋተኛውን በመለየት እርምጃ እንዲወስዱ መመሪያ መተላለፉን፣ በቀጣይ ተመሳሳይ ችግሮች እንዳይከሰቱ ለአሽከርካሪዎች ከፍተኛ ስልጠና እየተሰጠ እንደሆነና እርምጃው ለወደፊቱም በተጠናከረ መልኩ እንደሚቀጥል፤ በዓለም ገና ዲስትሪክት በተገቢው ሁኔታ ያልተያዙ የተሽከርካሪ ሞተሮች እና አካሎች በተመለከተ የተሽከርካሪ ሞተሮች በአብዛኛው ረጅም እድሜ ያላቸው መሆኑን እና ለማስወገድም በእንቅስቃሴ ላይ እንደሚገኙ፣ አካሎቻቸው የጎደሉ ተሽከርካሪዎችን የሚመለከታቸው ሠራተኞች ወይም ኃላፊዎች ከነበሩበት የሥራ ቦታ በመቀያየራቸው እንዲሁም ጊዜው ረጅም በመሆኑ መረጃ ማቅረብ አለመቻሉን፣ የስርቆት ሙከራ የተደረገባቸው ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ ጉዳዩ ለፀረ ሙስና መተላለፉን እና በአሁኑ ወቅት በቃሊቲና በዓለም ገና አካባቢ ከፍተኛ የፅዳት ዘመቻና የማስተካከል ሥራ እየተከናወነ እንደሆነና ንብረቶቹንም ለማስወገድ በሂደት ላይ እንደሆነ

በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ የኦዲት ቡድኑ ሥራውን አጠናቆ ከወጣ በኃላ ገልጸዋል፡፡ ሆኖም ከላይ ለተገለጹት ሁኔታዎች በወቅቱ መረጃ ተጠይቆ ባለመቅረቡ በመልሱ የተገለጹት እርምጃዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

59. በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር መ/ቤት፤

- ለባለበጀት መ/ቤቶች የተገዙ ሦስት አዳዲስ ተሽከርካሪዎች መጠባበቂያ ጎማዎቻቸው ተሰርቀው እያሉ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ስለ ጉዳዩ ውሳኔ ሳይሰጥበት ከነጉድለታቸው መ/ቤቶቹ በአስረካቢ ኮሚቴው አማካኝነት እንዲረከቡ የተደረገ ሲሆን፣ ጉዳዩን በተመለከተ መ/ቤቱ አስተዳደራዊ እርምጃ ስለመውሰዱ ማስረጃ አለመቅረቡ፤

- የሚኒስቴሩ ንብረት የሆነ የሠሌዳ ቁጥር 4-08027 ቶዮታ ራነር በ14/07/2002 ዓ.ም. ዋና ዋና የሞተር አካሎች መስረቃቸው ተጠቅሶ ለፖሊስ ሪፖርት የተደረገ ቢሆንም ለክስ የሚያበቃ በቂ መረጃ አልቀረበም በሚል የክስ መዝገቡ ለጊዜው እንዲዘጋ መደረጉን፣

- በሚኒስቴሩ በተደጋጋሚ የተሽከርካሪ መለዋወጫዎች፤ ዋና ዋና የሞተር አካሎችና የመጠባበቂያ ጎማዎች እየጠፉ ባለበት ሁኔታ የመ/ቤቱ ጥበቃዎች ያለ መ/ቤቱ ፈቃድ በሥራ ሰዓት የጥበቃ ቦታቸውን ክፍት አድርገው ለግል ጉዳያቸው ከመ/ቤቱ ግቢ ውጭ የሚሄዱ መሆኑ፣

- ለባለበጀት መ/ቤቶች የተገዙ አዳዲስ ተሽከርካሪዎች የተለያዩ መለዋወጫ ዕቃዎች ለመቆጣጠር በሚያዳግት ሁኔታ ከሚኒስቴሩ የተሽከርካሪ መለዋወጫ ዕቃዎች ጋር በአንድ መጋዘን አብረው ተቀምጠው መገኘታቸው፡፡

- በሚኒስቴሩ የሚገኝ የመለዋወጫ መጋዘን ንብረት አስተዳደር ሠራተኛ ስለ ተሽከርካሪ መለዋወጫዎች በቂ እውቀት የሌላቸው በመሆኑ የዕቃ ወጪ መጠየቂያ /ሞዴል 22/ አስሞልተው መለዋወጫ ለማውጣት የሚመጡ ሠራተኞች መጋዘኑ ውስጥ እንዲገቡ በማድረግ የተጠየቀውን

መለዋወጫ ዕቃ እራሳቸው ጠያቂዎቹ አንስተው እንዲወስዱ የሚደረግ መሆኑን፤ ለማወቅ ተችሏል፡፡

60. በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ጋራዥ በርካታ የመለዋወጫ ዕቃዎችና ለጥገና የገቡ ተሽከርካሪዎች ያሉ ቢሆንም ጋራዡ በጫካ የተዋጠ በመሆኑ ለጥበቃ የማያመች እና ለስርቆት የተጋለጠ መሆኑን በአካል በቦታው ተገኝቶ በማየት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

61. ስለሁኔታው የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የድጋፍና የሥራ ሂደቶች ማስተባበርያ ዳይሬክተር የተሽከርካሪዎቹ አካል መሰረቅን በተመለከተ የተቀመጠው ሁኔታ ትክክል መሆኑን ሆኖም ለክሱ የቀረቡ ማስረጃዎች በጥርጣሬ ላይ የተመሠረቱ ስለነበሩ እና እጅ ከፍንጅ የተያዘ መረጃ ባለመኖሩ የክስ ፋይሉ የተዘጋ መሆኑን፣ ለወደፊቱ የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት ጥበቃውን እንደሚያጠነክሩ፣ የመለዋወጫ መጋዘን ኃላፊ የሥራ መዝርዝሩ በሚያስቀምጠው መሠረት የማስተካከያ እርምጃ እንደሚወሰድ የገለጹ ሲሆን፣ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ወቅቱ ክረምት ስለነበር በገራዡ አካባቢ በጣም ያደገ ሣር በመኖሩ የተፈጠረ ሁኔታ መሆኑን እና በአሁኑ ወቅት እየታጨደ መሆኑን፤ በሂደት ጋራዡን ለመዝጋትና ቦታውንም ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለማስረከብ ዕቃዎችን የማንሳት እንቅስቃሴ መጀመራቸውን ገልጸዋል፡፡

62. የተሽከርካሪዎች መጥፋት፣ ከመ/ቤቶቹ እውቅና ውጭ መሸጥ፣ በአሽከርካሪዎች ጥንቃቄ ጉድለት ምክንያት የተሽከርካሪዎች መገልበጥ፣ ያልተወገዱ ተሽከርካሪ አካሎች በቦታቸው አለመገኘት፣ የተሽከርካሪ ሞተሮች መጥፋት እና የተሽከርካሪ ሞተሮች ጥንቃቄ በጎደለው ሁኔታ በወቅቱ ሳይወገዱ ለጸሐይ፣ ለዝናብና ለአቧራ ተጋልጠው መገኘት፣ የተሽከርካሪ መለዋወጫዎች አጠባበቅ ላይ ድክመት መታየቱ በጣም ከፍተኛ ዋጋ እና ግምት ያለው ሀብት ለብክንት እንዲዳረግ መንገድ የሚከፍት ከመሆኑም በላይ የመንግስት ተሽከርካሪዎች በኃላፊነት በተረከባቸው አካል በቂ ጥበቃ እየተደረገላቸው አለመሆኑን ያመለክታል፡፡

## የተሽከርካሪ ነዳጅና ቅባት አጠቃቀምን በተመለከተ፤

63. የመንግስት መ/ቤቶች የነዳጅ እና የቅባት አጠቃቀም ላይ ተገቢውን ቁጥጥር እና ክትትል ሊያደርጉ ይገባል፡፡

64. በማዕድን ሚኒስቴር የግዢ፤ ፋይናንስ እና ንብረት አስተዳደር የሥራ ሂደት ለስምንት ተሽከርካሪዎች ነዳጅና ቅባት ጥያቄ ሲቀርብለት የሚፈቅድ ቢሆንም፣ እነዚህ ተሽከርካሪዎች የሥራ ሂደቱ በቀጥታ የማይቆጣጠራቸው መሆኑን፤ በግብርና ሚኒስቴር የተሽከርካሪ ዘይት ወጪ ለማድረግ የሚያዘው እና የሚፈቅደው ዘይቱን በበርሜል ወጪ አድርጎ የተረከበው ሠራተኛ መሆኑን እና ሌላ የሚቆጣጠር አካል አለመኖሩን ከተሰበሰቡ መረጃዎች እና ቦታው ላይ በአካል በመገኘት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

65. በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ጋራዥ የሚገኝ የነዳጅ ማደያ በአንድ ሰው ብቻ አገልግሎት የሚሰጥ ሲሆን፣ የተፈቀደ ነዳጅ ወደ መኪኖቹ የመሙላት ተግባር ነዳጁን በጠየቁ ሹፌሮች ያለ ተቆጣጣሪ መከናወኑ፤ በ2001 በጀት ዓመት በሻኮሽ /ቀብሪ ደሀር/ አስፋልት ፕሮጀክት የ8315 ሌትር የናፍጣ ጉድለት የታየ መሆኑን፡፡ ይህም በስቶክ ካርድ ላይ ባለው የናፍጣ ዋጋ ሲሰላ የብር 74,085.70 (ሰባ አራት ሺህ ሰማንያ አምስት ብር ከሰባ ሣንቲም) ዋጋ ግምት እንዳለው፤ በአዲግራት ዲስትሪክት ሥር የነዳጅ ወጪ ትኬት ሳይፈረም ነዳጅ የሚወሰድበት ሁኔታ መኖሩን ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

66. ይህንንም በተመለከተ የሚመለከታቸው መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የማዕድን ሚኒስቴር ሚኒስትር ስምንቱ ተሽከርካሪዎች ሙሉ ለሙሉ የሚሰማሩት የተሽከርካሪ አስተዳደር በማይመለከተው በሌላ የሥራ ሂደት ሲሆን፣ የነዳጅ፣ የጥገና፣ የመድህን ዋስትና ወ.ዘ.ተ. የሚከናወነው ግን በግዥ፣ ፋይናንስ እና ንብረት አስተዳደር የሥራ ሂደት መሆኑን፤ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር በማዕከል መሳሪያዎች ጥገና ቅጥር ግቢ በሚገኘው የነዳጅ ማደያ አንድ የነዳጅ ስርጭት ፀሐፊና አንድ የጉልበት ሠራተኛ መመደባቸውን፣ የተፈቀደው ነዳጅ መጠን በተመደበው ረዳት እንደሚሞላ እና አልፎ አልፎ ነዳጁ በሹፌሮች ቢሞላም ረዳቱን የማገዝ ሥራ ከመሆን ውጪ አሠራሩን የላላ እንደማያደርገው፣ የነዳጅ ተቆጣጣሪዎም በቢሮዋ

ውስጥ ሆና በቅርብ ርቀት ለመመልከት እንደምትችል እና በቢሮዋ ውስጥ አጠገቧ የነዳጅ መክፈቻና መዝጊያ ስላላት ለመቆጣጠር የምትችል መሆኑን፣ በነዳጅ ማከማቻ ጋን ውስጥ የሚገኘው ቀሪ ከስቶክ ምዝገባ ጋር በየዕለቱ የሚገናዘብ እና የነዳጅ ስርጭት የማመዛዘን ተግባር እንደሚከናወን፤ በጉድለት የታየውን ነዳጅ በተመለከተ በወቅቱ በቀረበው የኦዲት ሪፖርት መሠረት ፕሮጀክቱ የማስተካከያ እና የዕርምት እርምጃ ወስዶ እንዲያሳውቅ መታዘዙን፣ ጉዳዩ በፕሮጀክቱ ዲሲፕሊን ኮሚቴ እየታየ መሆኑን እና ውጤቱን በቅርቡ እንዲሚያሳውቅ፤ የነዳጅ ወጪ ቲኬት ሳይፈረም ነዳጅ መውሰድን በተመለከተ ስህተቱን ለፈጸመው የሥራ ክፍልና በዲስትሪክቱ ሥር ለሚገኙ የሥራ ክፍሎች ተመሳሳይ ስህተት እንዳይከሰት መመሪያ የተሰጠ መሆኑን የዲስትሪክቱ ሥራ አስኪያጅ እንዳረጋገጡ የኦዲት ቡድኑ ሥራውን አጠናቆ ከወጣ በኃላ ዘግይተው ገልፀዋል፡፡ሆኖም በወቅቱ መረጃዎቹ ተጠይቀው ባለመቅረባቸው ተወስደዋል የተባሉትን እርምጃዎች ትክክለኝነትን ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

67. በእነዚህ የፌዴራል መ/ቤቶች የነዳጅና ቅባት አጠቃቀም፣ ቁጥጥር እና የተቀዳው ነዳጅ በትክክል ለመንግሥት ሥራ የዋለ መሆኑን በመከታተሉ ረገድ የጎላ ድክመት እንዳለ የሚያሳይ ሲሆን፣ የመንግስት መ/ቤቶች በሚያስተዳድሯቸው ተሽከርካሪዎች የነዳጅ እና ቅባት አጠቃቀም ላይ ተገቢው ቁጥጥር አለመደረጉ የነዳጅ ወጪ ከፍተኛ እንዲሆን የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ የስምሪት ሥርዓቱን ባልተከተለ ሁኔታ የተሽከርካሪ አስተዳደር በማይመከለተው ሌላ የሥራ ሂደት ብዛት ያላቸው ተሽከርካሪዎች እንዲተዳደሩ መደረጉ በተሽከርካሪ መረጃ አያያዝ ላይም ሆነ አጠቃቀም ላይ ክፍተት ይፈጥራል፡፡

## የመንግስት ተሽከርካሪዎች የመድን ዋስትናን በተመለከተ፤

68. የመንግስት መ/ቤቶች ለሚያስተዳድሯቸው ተሽከርካሪዎች የመድህን ዋስትና (insurance) እንዲኖራቸው ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

69. በመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን የመድህን ሽፋን ያልተገባላቸው ተሽከርካሪዎች መኖራቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህንንም በተመለከተ የባለስልጣኑ የድጋፍ ሰጪ ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ተሽከርካሪዎቹ

በእርጅና ምክንያት በመድህን ድርጅት ተቀባይነት ያጡ በመሆናቸው የመድህን ሽፋን ያልተገባላቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

70. አገልግሎት እየሰጡ ያሉ ተሽከርካሪዎች የመድህን ዋስትና ሽፋን ከሌላቸው በተለይም ያረጁ መኪናዎች ለአደጋ የመጋለጣቸው አጋጣሚ ሰፊ በመሆኑ መ/ቤቱን ላልተጠበቀ ከፍተኛ ወጪ ሊያጋልጠው የሚችል ከመሆኑም በላይ ነዳጅ በአግባቡ ስለማያቃጥሉ ለአካባቢ አየር መበከልም አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡

## የተሽከርካሪዎች የእሳት አደጋ ማጥፍያ መሣሪያን በተመለከተ፤

71. ማንኛውም የመንግስት ተሽከርካሪ የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሳሪያ (fire extinguisher) ሊኖረው ይገባል፡፡

72. በጤና ጥበቃ ሚኒስተር፣ በማዕድን ሚኒስተር፣ በውሃና ኢነርጅ ሚኒስተር፣ በግብርና ሚኒስተር እና በመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን የሚገኙ ተሽከርካሪዎች የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሳሪያ /Fire Extingusher/ ያላቸው ቢሆንም መሣሪያው መሥራትና አለመስራቱን በተመለከተ በየጊዜው ፍተሻ እንደማይደረግ እና አሽከርካሪዎች አጠቃቀሙን እንደማያውቁ ለማወቅ ተችሏል፡፡

73. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የውኃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሚኒስትር፣ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ እና የማዕድን ሚኒስቴር ሚኒስትር ሁኔታው ትክክል መሆኑን እና የማስተካከያ እርምጃ እንደሚወስዱ፤ የግብርና ሚኒስቴር የግዥ፣ ፋይናንስ እና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክተር ጥቂት ተሽከርካሪዎች ብቻ የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሳሪያ የሌላቸው መሆኑን እና በሂደት የማሟላት እና አጠቃቀሙንም በተመለከተ አሽከርካሪዎችን የማሰልጠን ሥራ ለመሥራት ማቀዳቸውን፤ የመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን የድጋፍ ሰጪ ዳይሬክተር በዕቅድ ተይዞ ወቅቱን ጠብቆ የማስተካከል ሥራ እንደሚያከናውኑ ገልጸዋል፡፡

74. ከዚህም በተጨማሪ መጠይቅ ከተላከላቸው እና ከመለሱ 33 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ውስጥ 11 መ/ቤቶች (33.33%) ተሽከርካሪዎቻቸው የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሳሪያ (fire extinguisher) የሌላቸው መሆናቸውን የገለጹ ሲሆን፣ 16 መ/ቤቶች (48.48%) ደግሞ የተሽከርካሪዎቻቸው የእሳት

አደጋ ማጥፊያ መሳሪያ (fire extinguisher) በትክክል አገልግሎት የሚሰጥ እና የማይሰጥ መሆኑን በተመለከተ ክትትል የማያደርጉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

75. አብዛኛዎቹ የመንግስት ተሽከርካሪዎች አዲስ ተገዝተው ሲገቡ አብሯቸው የሚገባ የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሳሪያ (fire extinguisher) ያላቸው ቢሆንም አጠቃቀማቸው የማይታወቅና ሲያልቁና ሲበላሹ እንዲሁም የአገልግሎት ጊዜያቸው ሲያበቃ በየወቅቱ ክትትል የማይደረግላቸው መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሳሪያ (fire extinguisher) አጠቃቀምን በተመለከተ ለአሽከርካሪዎች ስልጠና አለመሰጠቱ እና የእሳት ማጥፍያ መሳሪያዎቹ የአገልግሎት ጊዜ ላይ ክትትል አለመደረጉ ተሽከርካሪዎቹ ላይ ሊከሰት የሚችል የእሳት አደጋን በቀላሉ ለመከላከል እንዳይቻል ያደርጋል፡፡

## በመንግሥት ተሽከርካሪዎች ጎን በሮች ላይ የመ/ቤታቸው ዓርማ መለጠፍን በተመለከተ፤

76. የመንግስት መ/ቤቶች በሚያስተዳድሯቸው የመንግስት ተሽከርካሪዎች ሁለቱም የጎን በሮች ላይ የመ/ቤቱ ዓርማ መለጠፍ አለባቸው፡፡

77. በናሙና መርጠን ካየናቸው መ/ቤቶች ውስጥ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ በውኃና ኢነርጂ ሚኒስቴር፣ በግብርና ሚኒስቴር፣ በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና በመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን የሚገኙ ተሽከርካሪዎች በሁለቱ የጎን በሮቻቸው ላይ የመ/ቤታቸው ዓርማ እንዲለጠፍ አልተደረገም፡፡ ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የመ/ቤቶቹ የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ መ/ቤቱ የተለየ ዓርማ የሌለው መሆኑን፤ በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ የተሰጠው አስተያየት ትክክል መሆኑን፤ በግብርና ሚኒስቴር የግዥ፣ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክተር ቀደም ሲል የሚኒስቴሩ ተሽከርካሪዎች የጎን ዓርማ የነበራቸው እና ከቅርብ ዓመት ወዲህ ቢዘነጋም ለወደፊቱ አዲስ በተደራጀው የንብረት አስተዳደር የሥራ ሂደት ሊሠራበት ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን፤ በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ የተለመደ አሠራር አለመሆኑንና መ/ቤቱ የተለየ ዓርማ እንደሌለው ገልጸዋል፤

78. በመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን ድጋፍ ሰጪ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ባለሥልጣኑ በሚያስተዳድራቸው የመንግስት ተሽከርካሪዎች ላይ ዓርማ ማድረጉ ከመ/ቤቱ የሥራ ባህርይ አኳያ አስፈላጊነቱን ስላላመኑበት መሆኑን እና አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ለወደፊት ተጠንቶ ተግባራዊ እንደሚደረግ ገልፀዋል፡፡

79. ከዚህም በተጨማሪ መጠይቅ ከተላከላቸው እና ምላሽ ከሰጡ 33 የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ውስጥ 20 መ/ቤቶች (60.61%) ተሽከርካሪዎቻቸው በጎን በሮቻቸው ላይ የመ/ቤታቸውን ዓርማ እንዲለጥፉ አለመደረጉን ገልጸዋል፡፡

80. ይህን ጉዳይ አስመልክቶ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የመንግስት ንብረት አስተዳደርን በሚመሩት ሠነዶች ላይ ሁኔታው ያልተመለከተ በመሆኑ እስከአሁን በኤጀንሲው በኩል ክትትል አለመደረጉን እና አስፈላጊነቱ ከታመነበት ወደፊት ለተሽከርካሪ በተለይ በሚዘጋጀው መመሪያ ውስጥ እንዲካተት ሊደረግ እንደሚችል ገልጸዋል፡፡

81. በመንግሥት ተሽከርካሪዎች በሮች ላይ የመ/ቤቶች መለያ ዓርማ አለመለጠፉ ተሽከርካሪዎች የየትኛው መ/ቤት መሆናቸውን በመለየት ያልተፈቀደ አካባቢ ቢሄዱ፣ ባልተፈቀደለት አካል ቢሽከረከሩ፣ ከተመደበላቸው የመንግስት ዓላማ ውጪ አገልግሎት ቢሰጡ ወ.ዘ.ተ. ለመከታተል፣ ለመቆጣጠር እና ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ለማድረግ አያስችልም፡፡

# የመንግስት ተሽከርካሪዎች ጥገናን በተመለከተ

## የውጭ ጋራዥ የመምረጫ መስፈርትን በተመለከተ

82. የመንግስት ተሽከርካሪዎች ከመ/ቤቱ ውጭ በሆነ ጋራዥ መጠገን ካስፈለጋቸው ጥገና የሚያደርገውን ጋራዥ ለመምረጥ የሚያስችል መስፈርት ሊኖር ይገባል፡፡

83. በናሙና ተመርጠው ከታዩ መ/ቤቶች ውስጥ በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር፣ በውኃና ኢነርጂ

ሚኒስቴር እና በማዕድን ሚኒስቴር ከአቅም በላይ የሆኑ እና በራሳቸው ጋራዦች ሊጠገኑ የማይችሉ ብልሽቶች ሲገጥሙ ለተሽከርካሪዎች ተገቢውን ጥገና መስጠት የሚችል የውጭ ጋራዥ የመምረጫ መስፈርት እንደሌላቸው ታውቋል፡፡

84. ይህን በተመለከተ የሚመለከታቸው የመ/ቤቶች የሥራ ኃላፊዎች በቀረበላቸው የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ከዚህ የሚከተሉትን አስተያየቶች ሰጥተዋል፡፡ የማዕድን ሚኒስቴር ሚኒስትር እና በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የደጋፊ የሥራ ሂደቶች ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የተሻለ መለዋወጫና አገልግሎት ለማግኘት ተሽከርካሪዎቻቸውን በአስመጪ ኩባንያዎች እንደሚያስጠግኑ፤ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ እና የውሃ ሀብት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ የኦዲት ግኝቱ ትክክል እና የተቀበሉት መሆኑን፤ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ የውጭ ጋራዥ የመምረጫ መስፈርት እንደማያስፈልግ እና በመንግስት ግዥ ደንብ መሠረት የዕቃም ሆነ የጥገና የአገልግሎት ግዥ እንደሚፈጽሙ ገልጸዋል፡፡

85. ከዚህም በተጨማሪ መጠይቅ ተልኮላቸው ምላሽ ከሰጡ 33 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች መካከል 8 መ/ቤቶች (24.24%) ተሽከርካሪዎቻቸውን ከመ/ቤታቸው ጋራዥ ውጭ የጥገና አገልግሎት ለማግኘት የሚያስችል የውጭ ጋራዥ የመምረጫ መስፈርት እንደሌላቸው ገልጸዋል፡፡

86. ከዚህ ሁኔታ ለመገንዘብ የሚቻለው በውጭ ጋራዥ ጥገና ለሚደረግላቸው ተሽከርካሪዎች የመንግስት መ/ቤቶች የመምረጫ መስፈርት ሳይጠቀሙ እና የውጭ ጋራዦቹ የሚሰጡት የጥገና አገልግሎት የተሻለ ብቃት ያለው መሆኑ ሳይረጋገጥ ጥገና የሚደረግበት ሁኔታ መኖሩን ሲሆን፣ በአስመጪ ኩባንያ በኩል የጥገና አገልግሎት የሚሰጥበት ሁኔታም ቢሆን ከዋጋ አንፃር አዋጪ ስለመሆኑ የሚታይበት ሁኔታ እንደሌለ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ይህ ሁኔታ የመንግስት ተሽከርካሪዎች ጥገና ተገቢ የቴክኒክ ብቃት በሌላቸው ጋራዦች እንዲከናወን እና ለወጣው ወጪ ተመጣጣኝ አገልግሎት መገኘቱን ለማረጋገጥ እንዳይቻል መንገድ የሚከፍት በመሆኑ በተሽከርካሪዎቹ ላይ ተደጋጋሚ ብልሽት እንዲያጋጥም እና የመንግስት ገንዘብ አለአግባብ እንዲወጣ ያደርጋል፡፡

## የጥገና ጥያቄ የሚቀርብላቸው ተሽከርካሪዎች የደረሰባቸው ብልሽት እና የሚያስፈልጋቸው ጥገና በገለልተኛ አካል የሚረጋገጥ መሆኑን በተመለከተ፡

87. የመንግሥት ተሽከርካሪዎች ጥገና እንዲደረግላቸው ጥያቄ ሲቀርብ ጥገና ከመደረጉ በፊት የደረሰባቸው ብልሽት እና አስፈላጊው ጥገና ተሽከርካሪውን ከሚጠቀመው እና ጥገናውን ከሚያደርገው አካል ገለልተኛ በሆነ ባለሙያ ሊረጋገጥ እና በሚመለከተው የሥራ ኃላፊ ሊጸድቅ ይገባል፡፡

88. በናሙና ተመርጠው ከታዩ መ/ቤቶች ውስጥ በግብርና ሚኒስቴር የመ/ቤቱ የጋራዥ ኃላፊነት ና የቴክኒክ ኢንስፔክተርነት ተግባር በአንድ ሠራተኛ ተደርቦ የሚከናወን መሆኑን፤ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ በማዕድን ሚኒስቴር እና በመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን ተሽከርካሪዎች ጋራዥ ከመግባታቸው በፊት የደረሰባቸውን ብልሽት የሚያረጋግጥ ከጋራዥ ክፍሉ ገለልተኛ የሆነ ራሱን የቻለ የጥገና የቴክኒክ ኢንስፔክተር የሌለ መሆኑን፤ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒሰቴር ተሽከርካሪዎች ጥገና እንዲደረግላቸው ጋራዥ በሚገቡበት ወቅት መካኒኮች ተሽከርካሪውን የጥገና መረካከቢያ ቅጽ ሳይሞላ ከአሽከርካሪዎች የሚረከቡ መሆኑን፤ በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ተሽከርካሪዎች ለጥገና ወደ ጋራዥ ከመግባታቸው በፊት የደረሰባቸውን ብልሽት የሚያረጋግጥ የቴክኒክ ኢንስፔክተር ያለ ቢሆንም እንስፔክተሩ ተጠሪነቱ ለጋራዥ ኃላፊው መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

89. ይህንን በተመለከተ የሚመለከታቸው መ/ቤቶች የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የግብርና ሚኒስቴር የግዥ፣ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክተር የጥገና ተግባርን ለማስተባበር በአዲሱ አሠራር ከሠራተኛ መካከል ተመርጦ የብልሽት ሁኔታን የማጣራት ሥራ እንደሚከናወንና በሥራ መደብ ደረጃ የተመደበ ሠራተኛ እንደሌለ እና በአሁኑ ወቅት በጋራዥ ላይ እየተደረገ ያለው ጥናት እየተጠናቀቀ በመሆኑ ሁኔታው ሊስተካከል እንደሚችል፤ የማዕድን ሚኒስቴር ሚንስትር የመካኒክ እጥረት እንዳለባቸው እና ለወደፊቱ ገለልተኛ የሆነ የጥገና የቴክኒክ ኢኒስፔክተር እንደሚመድቡ፣ የመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን የድጋፍ ሰጪ ዳይሬክተር ተሽከርካሪዎቹ ወደ ጋራዥ ሲገቡ በሪሰፕሽን ሠራተኛ በኩል እንደሆነና ተጠግነው ሲወጡም ተሽከርካሪውን

ለጥገና የተረከበ ሰው መጠገኑን አረጋግጦ ለአሽከርሪው እንደሚያስረክብ ሆኖም የሠራተኛ እጥረት በሚኖርበት ጊዜ በጋራዥ ኃላፊው ወይም እሱ በሚወክለው መካኒክ እንደሚረጋገጥ፤ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የደጋፊ የሥራ ሂደቶች ማስተባበሪያ ዳይሬክተር ተሽከርካሪው በአግባቡ መጠገኑን የማረጋገጥ ተግባር ሊከናወን የሚገባው ጥገና ባከናወነው ኃላፊ መሆኑን፤ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሚንስትር ዴኤታ በመ/ቤቱ አወቃቀር የቴክኒክ ኢንስፔክተሩ ለጋራዥ ኃላፊው ተጠሪ እንዲሆን ተደርጎ የተሠራ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

90. በተመሳሳይ መልኩ ለተላከላቸው መጠይቅ ምላሽ ከሰጡ 33 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች መካከል 14 መ/ቤቶች (42.42%) ተሽከርካሪዎቻቸው ለጥገና ጋራዥ ከመግባታቸው በፊት የደረሰባቸውን ብልሽት የሚያረጋግጥ ገለልተኛ የቴክኒክ ኢንስፔክተር እንደሌላቸው ገልፀዋል፡፡

91. የመንግስት ተሽከርካሪዎች ለጥገና ጋራዥ በሚገቡበት ውቅት በትክክል ስለመበላሸታቸው የሚፈትሽ ገለልተኛ ቴክኒካል ኢንስፔክተር እንዲኖራቸው ካልተደረገ ተሽከርካሪዎች በትክክል ጥገና የሚያስፈልጋቸው መሆኑን ለማረጋገጥ፤ የሚያስፈልጋቸውን የመለዋወጫ አይነት እና ብዛት፤ ለጥገና የሚያስፈልጋቸው ወጪ እና የጥገና ጊዜን በአግባቡ ለማረጋገጥ እና ለመቆጣጠር አያስችልም፡፡ ይህም አላስፈላጊ ጥገና እንዲከናወን፣ በመለዋወጫ አጠቃቀም ላይ ብክነት እንዲፈጠር፣ ከሚፈለገው ጊዜ በላይ በጥገና ስም ተሽከርካሪዎች አገልግሎት ሳይሰጡ እንዲቆዩ የሚያደርግ እና ለብልሹ አሠራር በር የሚከፍት ይሆናል ፡፡

## ተሽከርካሪዎች ለጥገና ጋራዥ ሲገቡ ጥገናው የሚወስደው ጊዜ መወሰንን በተመለከተ

92. የመንግስት ተሽከርካሪዎች ለጥገና ጋራዥ በሚገቡበት ወቅት እንደብልሽቱ አይነት ጥገናው የሚወስደው የጊዜ ገደብ ሊቀመጥ እና በጊዜ ገደቡ መሠረት ተጠግነው አገልግሎት ላይ መዋል አለባቸው፡፡ በተቀመጠላቸው የጥገና ጊዜ ገደብ መሠረት ተጠግነው ካልወጡ ያልወጡበት ምክንያት ሊገለጽና የሚመለከተው የሥራ ኃላፊ ሁኔታውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

93. በናሙና ተመርጠው ከታዩ መ/ቤቶች ውስጥ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተበላሹ ተሽከርካሪዎች ጥገናቸው መቼ ተጀምሮ መቼ መጠናቀቅ እና ወደ ሥራ መመለስ እንዳለባቸው የሚያሳይ የጥገና ሥራ ጊዜ ገደብ እንደማይቀመጥ፤ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ በውኃና ኢነርጂ ሚኒስቴር እና በመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን ተሽከርካሪዎች ጥገናቸውን ጨርሰው ይወጣሉ ተብሎ በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ተጠግነው እንደማይወጡ፣ ለበርካታ ወራት በጋራዥ እንደሚቀመጡ እና ለተጨማሪ ብልሽት እየተዳረጉ እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል፡፡

94. በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ከባድ አደጋ ደርሶባቸው ጋራዥ የገቡ የተወሰኑ ተሽከርካሪዎች ለ43 ወራት ( ሦስት ዓመት ከሰባት ወራት) ጋራዥ የቆዩበት ሁኔታ እንዳለ፣ ጥገና የተደረገላቸው 53 ተሽከርካሪዎች በናሙና ተወስደው በአማካኝ 16.58 ወራት (1 አመት ከ4 ½ ወራት) ተጠግነው ሥራ ላይ እስኪውሉ ጋራዥ ውስጥ እንደሚቆዩ፤ በዚህም ምክንያት መ/ቤቱ ሥራውን ለማከናወን ስተሽከርካሪ ኪራይ የሚያወጣው ወጪ ከፍተኛ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

95. በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ብልሽት የደረሰባቸው ተሽከርካሪዎች ከመ/ቤቱ ጋራዥ ውጭ እንዲጠገኑ /out source/ ተደረገው በበጀት እጥረት ምክንያት በወቅቱ ተጠግነው የሚፈለገውን አገልግሎት ሳይሰጡ ለበርካታ ወራት በጋራዥ ውስጥ ቆመው የሚገኙ መሆኑን ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

96. ስለሁኔታው የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒሰቴር የግዥና ፋይናንስ ንብረት አስተዳደር ዳይሬክተር ለወደፊቱ በተሰጠው አስተያየት መሠረት እንደሚያስተካክሉ፤ የውኃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ የጥገና በጀታቸው ተመጣጣኝ አለመሆን፤ መለዋወጫ አልፎ አልፎ አለመገኘት፤ የግዢ አቅርቦቱ ፈጣን አለመሆን እና ተሽከርካሪዎቻቸው በብዛት መስክ የሚቆዩ መሆናቸውን፤ የመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን የድጋፍ ሰጪ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የመካኒኮች እጥረት እና መለዋወጫዎች በገበያ ላይ አለመገኘት እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

97. የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ሥራቸው አገሪቱን ከጫፍ እስከ ጫፍ ማዳረስ የሚጠይቅ መሆኑና ካላቸው የተሽከርካሪ ቁጥር አንፃር ጋራዥ የቆሙ ተሽከርካሪዎች ብዙ አለመሆናቸውን፣ ከመንግስት በተጨማሪ ከአጋሮች ከሚገኝ ድጋፍ ለሎጀስትክስ ተብሎ የሚያዝ በጀት በመኖሩ በበጀት እጥረት ሳይጠገን የሚቆም ተሽከርካሪ እንደሌለ፣ የቆሙትም ጥገናውን በሚያከናውነው ኩባንያ ተራ የተያዘላቸው እንደሚሆኑ የገለጹ ቢሆንም ይህን ሁኔታ የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡

98. የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት ማዕከላዊ ጋራዥ በነበረው መዋቅር የተሽከርካሪዎች ብዛትና የአደጋው መበራከት በሚፈለገው የጥገና ፍጥነት ማስተናገድ አለመቻል፣ ስራውን ለውጭ ጋራዦች ለመስጠት ከዚህ በፊት የታየ ተሞክሮ ውጤታማ እንዳልነበረ ሆኖም በአሁኑ ጊዜ ይህን ችግር ለመፍታት ከመከላከያ ሚኒስቴር የሎጅስቲክ መምሪያ ጋር ድርድር ተደርጎ በተወሰነ ደረጃ መሻሻል እየታየ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

99. ከላይ ከተገለጹት ሁኔታዎች እና ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለመረዳት እንደተቻለው ጥገና የሚደረግላቸው ተሽከርካሪዎች ያጋጠማቸው ብልሽት ክብደት ታይቶ የጥገና የጊዜ ገደብ እንደማይቀመጥላቸው፣ የጥገና የጊዜ ገደብ የተቀመጠላቸውም ቢሆኑ የተቀመጠላቸውን ጊዜ ጠብቀው ተጠግነው ወደ ሥራ እንደማይሰማሩ እንዲሁም ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ በላይ ለወሰዱ ጥገናዎች በቂ ምክንያት እንደማይቀርብ ለመገንዘብ የተቻለ ሲሆን፣ ይህም ሁኔታ ተሽከርካሪዎቹ ለተጨማሪ ብልሽት እንዲዳረጉ የሚያደርግ ከመሆኑን በላይ በእነዚህ ተሽከርካሪዎች ይሠሩ የነበሩ ሥራዎችን ለማሠራት ሌሎች ተሽከርካሪዎችን በመከራየት ከፍተኛ ወጪ እንዲወጣ የሚያደርግ መሆኑን ነው፡፡

## የተሽከርካሪዎች አቀማመጥን በተመለከተ፤

100. አገልግሎት የሚሰጡ፣ ለጊዜው ተበላሽተው ጥገና በመጠባበቅ ላይ ያሉ እና ፈጽሞ አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የመንግሥት ተሽከርካሪዎች ተለይተው መቀመጥ አለባቸው፡፡

101. በትራንስፖርት ባለስልጣን፣ በግብርና ሚኒስቴር እና በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር እንዲወገዱ የተለዩ ተሽከርካሪዎች ጋራዥ ለጥገና ከገቡ ተሽከርካሪዎች ጋር አብረው ተቀላቅለው ተገኝተዋል፡፡ ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን የድጋፍ ሰጪ ዳይሬክተር በባለሥልጣኑ በተካሄደው የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት ምክንያት ሊወገዱ የሚገባቸው ተሽከርካሪዎችን የማስወገዱ ተግባር እንደዘገየ ሆኖም በአሁኑ ወቅት ቅድመ ዝግጅቶች ስለተጠናቀቁ በመመሪያው መሠረት ተሽከርካሪዎች እንደሚወገዱ፣ የውኃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ሁኔታው ትክክል መሆኑን፣ የግብርና ሚኒስቴር የግዥ፣ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክተር በተሽከርካሪዎቹ ላይ የደረሰው ብልሽት በጣም የከፋ ባለመሆኑ እና ክልልና ኮሌጆች አስጠግነው ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ ተሽከርካሪዎች በመሆናቸው ይህንኑ ታሳቢ በማድረግ በጋራዥ ውስጥ እንዲቆዩ መደረጉን ገልፀዋል፡፡

102. ስለጉዳዩ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ይህ ድክመት የፖሊሲ ሳይሆን የአፈጻጸም ችግር እንደሆነ እና የተሽከርካሪ ማስወገድ ጉዳይ አዲስ በተቋቋመው የመንግስት ንብረት አስወጋጅ ኮሚቴ /አካል/ ሲከናወን አብሮ እንደሚፈታ ዕምነት እንዳላቸው ገልጸዋል፡፡

103. ሊወገዱ የተዘጋጁ ተሽከርካሪዎች በጥገና ላይ ከሚገኙ እና አገልግሎት ከሚሰጡ ተሽከርካሪዎች ተለይተው የሚቀመጡበት ሁኔታ ካልተመቻቸ የተሽከርካሪዎቹ አካላት ለስርቆት እና ለብክነት እንዲጋለጡ መንገድ የሚከፍት ይሆናል፡፡

# የመንግስት ተሽከርካሪዎች አወጋገድን በተመለከተ

## ተሽከርካሪዎች ማገልገል ያለባቸውን ዘመን በተመለከተ

104. በሀገር አቀፍ ደረጃ አንድ የመንግስት ተሽከርካሪ ምን ያህል ዘመን ሊያገለግል እንደሚችል በጥናት ሊወሰን ይገባል፡፡

105. በናሙና መርጠን ከተመለከትናቸው መ/ቤቶች በማዕድን ሚኒስቴር፣ በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ በውኃና ኢነርጂ ሚኒስቴር፣ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እና በመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን የተሽከርካሪዎች

የአገልገሎት ዘመን ምን ያህል እንደሆነ በጥናት በተደገፈ መረጃ እንዲታወቅ አልተደረገም፡፡ ስለጉዳዩ በመ/ቤቶቹ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የደጋፊ የሥራ ሂደቶች ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ይህን ሁኔታ በተመለከተ የተዘጋጀ አገር አቀፍ ማንዋል ስለሌለ የተወሰኑ ተሽከርካሪዎቻቸው ያገለገሉ እንኳ ቢሆኑም ከማስወገድ ይልቅ ባላቸው ውስን በጀት እያስጠገኑ መጠቀም እንደአማራጭ እንደሚወስዱ፤ የውኃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ በመ/ቤቱ ደረጃ የተጠና ጥናት እንደሌለ ሆኖም ተሽከርካሪዎች በአማካኝ ከ6-8 ዓመታት የእርጅና ቅናሽ እንደሚያደርጉ እና የሚያስወግዱአቸው ተሽከርከሪዎች ከ18 ዓመታት በላይ ያገለገሉና የተጎዱ መሆናቸውን፤ የማዕድን ሚኒስቴር ምኒስትር ቀደም ባሉ ዓመታት በደንቡ መሠረት ያገለገሉ ተሽከርካሪዎችን በማስወገድ የሽያጩ ገቢ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፈሰስ የተደረገ ቢሆንም በምትኩ አንድ ተሽከርካሪ እንኳ ስላልተላከላቸው የተወሰኑ ተሽከርካሪዎች ከማስወገድ ይልቅ ባላቸው ውስን በጀት እያስጠገኑ መጠቀም እንደአማራጭ መውሰዳቸውን፤ የትራንስፖርት ባለስልጣን የድጋፍ ሰጪ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በተለያዩ ጥናቶች ውስጥ አመላካች ሁኔታዎች ቢኖሩም እራሱን የቻለ ጥናት አለማድረጋቸውን የገለጹ ሲሆን፣ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በዚህ ጉዳይ ላይ መልስ አልሰጠም፤

106. መጠይቅ ተልኮላቸው ምላሽ ከሰጡ 33 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች መካከል 26 መ/ቤቶች (78.79%) የሚያስተዳድሯቸው ተሽከርካሪዎች ምን ያህል ጊዜ ማገልገል እንደሚገባቸው በጥናት ላይ በመመስረት እንዲታወቅ አለማድረጋቸውን ገልፀዋል፡፡

107. ስለጉዳዩ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በመሠረቱ የአንድ ተሽከርካሪ የአገልግሎት ዘመን (Life Time) የሚወሰነው በየአምራች ኩባንያዎቹ መሆኑን፤ ለመንግስት ንብረት አመዘጋገብ እና የእርጅና ቅናሽ (Depreciation) ዓላማ የተሽከርካሪ እድሜ 5 ዓመት እንደሆነ በመንግሥት ቋሚ ንብረት አስተዳደር ማንዋል ላይ የተመለከተ ቢሆንም ለመንግሥት ተሽከርካሪዎች ማስወገድ ተግባር

እንደማያገለግል፤ የተሽከርካሪ የአገልግሎት ዘመን ከተሽከርካሪው አጠባበቅ እና ከሚሽከረከርበት ቦታ እንዲሁም አጠቃቀም ጋር የተያያዘ በመሆኑ አንድ ወጥ በሆነ መንገድ የመንግሥት ተሽከርካሪዎች የአገልግሎት ዘመን ይሄን ያህል ነው ብሎ መወሰን ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንጻር እንደማያስኬድ ገልጸዋል፡፡

108. የመንግስት ተሽከርካሪዎች ያገልገሎት ዘመን ለመወሰን የሚያስችል መመሪያ ባለመኖሩ፤መ/ቤቶቹ ካላቸው የተሽከርካሪ እጥረት እና ያስወገዱቸውን ተሽከርካሪዎች ለመተካት በወቅቱ ስለማይገዛላቸው ያሏቸውን ተሽከርካሪዎች ያለጊዜ ገደብ ደጋግመው እንደሚጠቀሙ ታውቋል፡፡ ይህ ሁኔታ ተሽከርካሪዎች ረጅም ጊዜ በማገልገላቸው ምክንያት የሚጠይቁት የነዳጅና የጥገና ወጪ ከሚሰጡት አገልግሎት ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ የሚሆን፣ በሰውና በንብረት ላይ አደጋ የማድረስ እድላቸው የሰፋ እንዲሆን የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ ተሽከርካሪዎቹ በሚያወጡት ከፍተኛ በአግባቡ ያልተቃጠለ ጭስ አካባቢን በስፋት የሚበክሉበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

## የተሽከርካሪ አስወጋጅ ኮሚቴ  መሰየምን በተመለከተ፤

109. በንብረት አወጋገድ መመሪያው መሠረት በመንግስት መ/ቤቶች ቢያንስ ሶስት አባላት ያለው የተሽከርካሪ አስወጋጅ ኮሚቴ በበላይ ኀላፊ መሰየም ይኖርበታል፡፡

110. መጠይቅ ከተላከላቸው 33 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች 10 መ/ቤቶች (30.30%) በመንግስት ንብረት አወጋገድ መመሪያ መሠረት ቢየንስ 3 አባላት ያሉት የተሽከርካሪ አስወጋጅ ኮሚቴ በመ/ቤታቸው የበላይ ኀላፊ እንዳልተሰየመ ገልፀዋል፡፡

111. እያንዳንዱ የመንግስት መ/ቤት በንብረት አወጋገድ መመሪያው መሠረት የአስወጋጅ ኮሚቴ ማቋቋም ካልቻለ እንዲወገዱ ለተጠየቁ ተሽከርካሪዎች የማስወገጃ መጠይቆች፤ መረጃዎች እና ሰነዶች ተሟልተው መቅረባቸውን የሚያረጋግጥ፤ ያልተሟሉ ካሉ ተሟልተው እንዲቀርቡ የሚያደርግ፤ በማስወገጃ መመዘኛዎች  እና በማስወገጃ መንገዶች መሠረት የሚቀርቡ ሰነዶችን የሚገመግም፤ በግምገማው መሠረት የውሳኔ ሃሳብ ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የሚያቀርብ እና እንዲሸጡ ውሳኔ የተሰጠባቸውን ተሽከርካሪዎች የጨረታ መነሻ

ዋጋ የመተመን ተግባራትን በወቅቱ የሚያከናውን አካል ስለማይኖር የተሽከርካሪዎች አወጋገድ በአግባቡ እንዳይከናወን ያደርጋል::

## የሚወገዱ ተሽከርካሪዎችን ዝርዝር እና ያሉበትን ሁኔታ የሚገልጽ መረጃን በተመለከተ

112. የሚወገዱ የመንግሥት ተሽከርካሪዎችን የሚያስወግደው አካል ሊወገዱ የሚገባቸውን ተሽከርካሪዎች ዝርዝር አጠቃላይ ሁኔታ የያዘ እና የተጠናቀረ መረጃ ሊኖረው ይገባል፡፡

113. የግብርና ሚኒስቴር በ1997ዓ.ም 116 ተሽከርካሪዎች ያስወገደ ቢሆንም ተሽከርካሪዎቹ በመመሪያው መሠረት ስለመወገዳቸው የሚያስረዳ መረጃ አልቀረበም፡፡ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በ2002 ዓ.ም ያስወገዳቸው 6 ተሽከርካሪዎች በንብረት አወጋገድ መመሪያ መሠረት የተወገዱ መሆኑን ለማረጋገጥ የተወገዱት ተሽከርካሪዎች መረጃ ተጠይቆ ተሽከርካሪዎቹ እንዲወገዱ ለአስወጋጅ ኮሚቴ ከተፃፈ ደብዳቤና የጨረታ መነሻ ዋጋ ማስታወቂያ በስተቀር በትክክል መወገድ የሚገባቸው ተሽከርካሪዎች የተወገዱ መሆናቸውን የሚያስረዳ መረጃ ሊያቀርቡ አልቻሉም፡፡

114. ይህንንም በተመለከተ የግብርና ሚኒስቴር ግዥ፣ ፋይናንስ እና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክተር በነባራዊ ሁኔታዎች መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት የእነዚህ የተወገዱ ተሽከርካሪዎች አወጋገድ መረጃ ያለ ቢሆንም መ/ቤታቸው ባደረገው የቢሮ ለውጥ ሳቢያ ተፈላጊ መረጃዎቹ ከፋይናንስ ሰነድ ጋር ተያይዘው በአንድ ቦታ ላይ ስለተከማቹ በአጭር ጊዜ ማቅረብ አለመቻላቸውን ሆኖም ወደፊት የሰነድ ማስቀመጫው ቦታው ሲደራጅ ማቅረብ እንደሚችሉ ገልፀዋል፡፡

115. የማዕድን ሚኒስቴር በ2001ዓ.ም ያስወገዳቸው 37 ተሽከርካሪዎች በምን ደረጃ ላይ እንደነበሩ በተሽከርካሪዎቹ አካል ላይ ያለና የሌለ ክፍል በቴክኒክ ባለሙያ የተገለፀ ቢሆንም ተሽከርካሪዎቹ ተጠግነው ሥራ ላይ የሚውሉ መሆን አለመሆናቸውን፣ ተሽከርካሪዎቹ እንዲወገዱ የተደረገበት ምክንያት፣ በምን መልኩ መወገድ እንዳለባቸው ማለትም ባሉበት ሁኔታ (as they are) ወይም በቁርጥራጭ (scrap) መልክ... ወዘተ በግልፀ አልተቀመጠም፡፡

116. ይህንን በተመለከተ የመ/ቤቱ ሚኒስትር በቀረበላቸው የነባራዊ ሁኔታዎች መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት በኦዲት ግኝቱና በተሰጠው አስተያየት መሠረት ወደፊት የታዩት ክፍተቶች ለማስተካከል ጥረት እንደሚደረግ ገላፀዋል፡፡

117. መጠይቅ ተልኮላቸው ምላሽ ከሰጡ 33 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች 7 መ/ቤቶች (21.21%) የሚወገዱ ተሽከርካሪዎችን ለማስወገድ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ለመ/ቤታቸው አስወጋጅ ኮሚቴ እንደማያቀርቡ ገልፀዋል፡፡

118. ከተሰበሰቡ መረጃዎች የመንግስት መ/ቤቶች የሚወገዱ የመንግስት ተሽከርካሪዎችን ለማስወገድ የሚረዱ ዝርዝር መረጃዎችን ማለትም የተሽከርካሪው ሞዴል፣ የተሠራበትና የተገዛበት ዘመን፣ የተገዛበት ዋጋ፤ የቻሲ፣ የሞተርና የሰሌዳ ቁጥሮች፣ የነዳጅ አይነት፣ ለጥገና የወጣው ወጪ፣ አገልግሎት ያቋረጠበት ምክንያትና ጊዜ በተሟላ መልኩ አጠናቅረው እንደማያደራጁና ለአስወጋጅ ኮሚቴው እንደማያስረክቡ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

119. የመንግስት መ/ቤቶች የሚወገዱ የመንግስት ተሽከርካሪዎችን ዝርዝር መረጃ አጠናቅረው ለአስወጋጅ ኮሚቴው አለማቅረባቸው መወገድ የሚገባቸው ተሽከርካሪዎች ባላቸው ሁኔታ መሠረት ተመጣጣኝ እና የተሻለ ዋጋ አውጥተው እንዲወገዱ ለማድረግ እንዳይቻል ያደርገዋል፡፡

## ሊወገዱ የሚገባቸው ተሽከርካሪዎች በወቅቱ መወገዳቸውን በተመለከተ

120. አንድ የመንግስት ተሽከርካሪ ከሚሰጠው አገልግሎት በላይ ወጪ የሚያስወጣ ወይም አገልግሎት መስጠት የማይችል ከሆነ በወቅቱ መወገድ አለበት፡፡

121. በውኃና ኢነርጂ ሚኒስቴር፣ በግብርና ሚኒስቴር እና በመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን ሊወገዱ የተለዩ ብዛት ያላቸው ተሽከርካሪዎች በወቅቱ ሳይወገዱ በጋራዥና በቃሊቲ ለፀሀይ፤ ለዝናብ፤ ለአቧራ ተጋልጠው እና ሳር በቅሎባቸው ተገኝተዋል፡፡ ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው መ/ቤቶች የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የውኃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ የኦዲት ግኝቱ ትክክል መሆኑን፤ የግብርና ሚኒስቴር ግዥ፣ ፋይናንስ እና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክተር የሚወገዱ ተሽከርካሪዎች የመለየት እና ቦታ ለይቶ የማስቀመጥ ሥራ እንደተጠናቀቀና የማስወገድ ሥርዓት በግዥ ኤጀንሲ

በኩል እንደሚፈፀም ታሳቢ አድርገው በመጠባበቅ ላይ እንደሆኑ፤ የትራንስፖርት ባለስልጣን የድጋፍ ሰጪ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር መ/ቤቱ ባካሄደው የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት ምክንያት እንደዘገየ እና በአሁኑ ወቅት ቅድመ ዝግጅቶች በመጠናቀቅ ላይ በመሆኑ በመመሪያው መሠረት ተሸከርካሪዎችን እንዲወገዱ እንደሚያደርጉ ገልፀዋል፡፡

122. በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን በቃሊቲ እና በዓለም ገና ዲስትሪክት በርካታ ተሽከርካሪዎች፣ ሞተሮቻቸው እና ዋና ዋና አካሎቻቸው ለፀሐይ፣ ለዝናብ እና ለአቧራ ተጋልጠው በወቅቱ ሳይወገዱ ሳር በቅሎባቸው የተገኙ ሲሆን፣ የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት በአሁኑ ወቅት ባለሥልጣኑ ቃሊቲና ዓለምገና አካባቢ ከፍተኛ የጽዳት ዘመቻና የማስተካከል ሥራ እያከናወነ እና ተሽከርካሪዎቹንም ለማስወገድ በሂደት ላይ እንደሆኑ ገልጸዋል፡፡



**ምስል 3. በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን በቃሊቲ ለፀሀይ፤ ለዝናብ እና ለአቧራ ተጋልጠው የሚገኙ ተሽከርካሪዎች**

123. **ስለጉዳዩ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ተሽከርካሪ በሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር** 184/2002 **በተቋቋመው የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ተጠቃለው ሊወገዱ ከታሰቡት ንብረቶች ውስጥ ስለሚገኝ በቅርቡ መፍትሔ እንደሚያገኝ ጠቅሰው ኤጀንሲው የንብረት ኦዲት ማካሄድ የጀመረው በቅርቡ በመሆኑ እና አብዛኞቹ መ/ቤቶች በኦዲት አለመሸፈናቸውን ሆኖም ለወደፊቱ**

የመንግስት መ/ቤቶች መወገድ የሚገባቸውን ተሽከርካሪዎች ማስወገድ አለማስወገዳቸውን እንደሚከታተሉ ገልጸዋል፡፡

124. ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለመገንዘብ የተቻለው የመንግስት ተሽከርካሪዎች በልዩ ልዩ ምክንያት ከአገልግሎት ውጪ ሲሆኑ ወይም አገልግሎት በብቃት መስጠት የማይችሉበት ደረጃ ላይ ሲደርሱ በንብረት አወጋገድ መመሪያው መሠረት ወቅታዊ እርምጃ ሊወሰድ የሚገባ ቢሆንም በየመ/ቤቱ በርካታ መወገድ የሚገባቸው የመንግስት ተሽከርካሪዎች ለፀሀይ እና ለዝናብ ተጋልጠው በአቧራ ተሸፍነውና ሳር በቅሎባቸው ለረዥም ዓመታት ሳይወገዱ ለብክነት ተዳርገው እንደሚገኙ ነው፡፡

125. የመንግሥት ተሽከርካሪዎች በተለያየ ምክንያት ማለትም ከሚሰጡት አገልግሎት ወጪያቸው የሚያመዝን ከሆነ፣ የመለዋወጫ እቃ ካልተገኘላቸው፣ ወ.ዘ.ተ...፣ ሁኔታው ተገምግሞ በወቅቱ ሊወገዱ የሚችሉበት ሁኔታ ካልተመቻቸ እና ለረጅም ጊዜ በአግባቡ ሳይጠበቁ ከተቀመጡ ተሽከርካሪዎቹ ለከፍተኛ ጉዳት ስለሚዳረጉ የሚያወጡት ዋጋ ዝቅተኛ እንዲሆን ከማድረጉም በላይ ለተለያየ አገልግሎት ሊውሉ የሚችሉ እጅግ ሰፋፊ የመንግስት ቦታዎችን በመያዝ ለልማት ሥራ እንዳይውሉ እና ለጥበቃ ተግባር አለአግባብ ወጪ እንዲወጣ ያደርጋል፡፡

## የተወገዱ ተሽከርካሪዎች በመመሪያው መሠረት የተወገዱ መሆኑን በተመለከተ

126. በጨረታ፣ በሀራጅ እና በዝውውር የሚወገዱ የመንግስት ተሽከርካሪዎች በአወጋገድ መመሪያው መሠረት ሊወገዱ ይገባል፡፡

127. የመንግስት ተሽከርካሪዎች በጨረታ ሲወገዱ የተለየ የጨረታ ሳጥን ማዘጋጀት እንዳለበት በጨረታ መመሪያው ቢደነገግም የማዕድን ሚኒስቴር በ2001ዓ.ም 37 ተሽከርካሪዎችን በጨረታ እንዲወገዱ ሲያደርግ አስወጋጅ ኮሚቴው የጨረታ ሳጥን ያለዘጋጀ በመሆኑ በጨረታ እንዲሸጡ የተወሰነባቸው ተሽከርካሪዎች በሀራጅ እንዲሸጡ ተደርገዋል፡፡ ተሽከርካሪዎች በጨረታ ሲወገዱ የተጫራቾች ስምና የመጫረቻ ዋጋ የአስወጋጅ ኮሚቴው በግልጽ ማንበብና መዝግቦ መያዝ እንዳለበት የጨረታ መመሪያው ቢያዝም ይህ

ተደርጎ አልተገኘም፡፡ የተሸጡ የመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች ከፍተኛ ዋጋ ላቀረቡ ተጫራቾች ስለመሸጣቸው የሚያሳይ መረጃ ተጠይቆ ሊቀርብ አልቻለም፡፡

128. በውኃና ኢነርጂ ሚኒስቴር በ2000 በጀት ዓመት ያስወገዳቸው ተሽከርካሪዎች ማስወገጃ ቅፀ ላይ እንደተገለፀው የተሽከርካሪዎቹ የተለያዩ አካላት (ሞተር፤ ጎማ ቸርኬ፤ ስታርተር፤ ካርቡሬተር፤ ወዘተ...) በተሸከርካሪው አካል ላይ አለመኖራቸው የተገለፀ ቢሆንም የሥራ አመራሩ ለጉዳዩ ምንም እርምጃ ሳይወስድበት እና እልባት ሳይሰጥ ተሽከርካሪዎቹ ባሉበት ሁኔታ ተወግደዋል፡፡

129. በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን በድሬዳዋ ዲስትሪክት የባለሥልጣኑ ንብረት የሆኑ ተሽከርካሪዎች የተሠራላቸው የማስወገጃ ሰነድ እንደሚያመለክተው ሞተሮቻቸውን ጨምሮ ዋና ዋና አካሎቻቸው በቦታው እንዳልተገኙ የሚያሳይ ቢሆንም ተሽከርካሪዎቹ ከነጉድለቶቻቸው በውዳቂ ብረታ ብረትነት መወገዳቸውን ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ መ/ቤቱ ሞተሮቻቸው ሳይኖሩ ከነጉድለታቸው እንዲሸጡ ስለተደረጉት ተሽከርካሪዎች የወሰደው አስተዳደራዊ እርምጃ እንዳለ ተጠይቆ ይህን የሚያሳይ መረጃ አላቀረበም፡፡

130. የማዕድን ሚኒስትር በቀረበላቸው የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት ሚኒስቴሩ እስካሁን ባለው አካሄድ ተሽከርካሪን ጨምሮ ማንኛውንም ቋሚ እቃ ሲያስወግድ የጨረታ ሳጥን እንደማይዘጋጅና ተወዳዳሪዎች በተገኙበት በገማች ኮሚቴ የተገመተውን ግምት መነሻ በማድረግ በቃል ዋጋዎችን በማወዳደርና ከፍተኛ ዋጋ ያቀረበውን በመምረጥ እንደሚከናወን እና፤ በጨረታም ተወስኖ በሀራጅ የተሸጡ ተሽከርካሪዎች መኖራቸውን ተቀብለው ወደፊት በመመሪያው መሠረት ለመሥራት ጥረት እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡

131. የውኃና ኢነርጂ ሚኒስትር ዴኤታ በቀረበላቸው የነባራዊ ሁኔት መግለጫ ላይ ሁኔታውን በተመለከተ በሰጡት አስተያየት የቀረበው ሃሳብ ትክክል መሆኑን፣ ነገር ግን በወቅቱ የነበሩት የአመራር አካላት ጉዳዩን ለማጣራት ጥረት ማድረጋቸውን ለመጥቀስ ሞተሩ በላዩ ያልተገኘበት ኮስትር ባስ 4-05818 በቀድሞ መንግስት ዘመን ሞተሩ ለጥገና የግል ጋራዥ ገብቶ የነበረ ሲሆን፣

የመኪናውን ሞተር ለማምጣት በተደረገው ጥረት ጋራዡ ዳቦ ቤት መሆኑና ባለጋራዡም አገር ውስጥ አለመኖሩ ተረጋግጦ አውቶቢሱ ባለበት ሁኔታ እንዲወገድ መወሰኑን፤ የሰሌዳ ቁጥራቸው 4-12635 እና 4-12660 የሆኑ ሱዚኪ መኪናዎች እንዲሁ ሳካ በሚባል የግል ጋራዥ ለጥገና ገብተው በ1983 የበቅሎ ቤት ፍንዳታ ጊዜ የተጎዱና የተዘረፉ በመሆናቸው ንብረቶቹ ባሉበት ሁኔታ እንዲመለሱ መደረጉን፤ በአጠቃላይ ንብረቶቹ እንደንብረት ባሉበት ሁኔታ ወደ መ/ቤቱ ይሰባሰቡ እንጂ መ/ቤቱ ሲገለገሉባቸው ቆይተው በአሠራር ችግር መረጃ የታጣላቸው እንዳልሆኑ ገልፀዋል፡፡

132. የማዕድን ሚኒስትር በቀረበላቸው የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ሁኔታውን በተመለከተ በሰጡት አስተያየት እየተሠራበት ያለው አሠራር በተገለፀው መሠረት እንደሆነ የተቀበሉት መሆኑን የገለጹ ሲሆን፣ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ዋና ሥራ አሥኪያጅ በቀረበላቸው የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት ተሸከርካሪ የማሰወገድ ሂደት ሲከናወን ተሸከርካሪውን የሚመለከት ዝርዝር መረጃ በተሸከርካሪ ማስወገጃ ቅጽ ላይ በሥራ ክፍሉ ተመዝግቦ በየደረጃው ጸድቆ ለመጨረሻ ውሳኔ ሲቀርብ ከተሸከርካሪዎቹ ላይ የጎደሉ ዋና ዋና አካላት ካሉ ለምን እንደጎደሉ ጥያቄ የሚቀርብ ቢሆንም ተጠያቂውን ለማቅረብ ሠራተኞች ወይም ኃላፊዎች በመቀያየራቸው እና ጊዜው ረጅም በመሆኑ መረጃ ለማቅረብ አለመቻሉን፣ ተሸከርካሪዎቹ ሳይወገዱ ቢቀር ዋጋቸው እየቀነሰ ስለሚሄድ እና ቀሪ አካላቸው የበለጠ ስለሚጎዳ ባለሥልጣኑን ለተጨማሪ ወጪ እንዳይዳርጉት በማሰብ መከናወኑን ገልጸዋል፡፡

133. መጠይቅ ተልኮላቸው ምላሽ ከሰጡ 33 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች 12 መ/ቤቶች (36.36%) ሊወገዱ የሚገባቸውን የመንግስት ተሸከርካሪዎች ለማስወገድ የተዘጋጀ የአወጋገድ መመሪያ የሌላቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

134. ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለመገንዘብ የተቻለው የሚወገዱ ተሸከርካሪዎች የመንግስት ንብረት አወጋገድ መመሪያን ባልተከተለ ሁኔታ የሚወገዱበት ሁኔታ መኖሩን፣ በዚህ ጉዳይ ላይ ክትትል እንደማይደረግ እና መ/ቤቶች የሚያስወገዷቸው ተሸከርካሪዎች አወጋገድ ክንውንን የሚገልጹ መረጃዎች በአግባቡ አጠናቅረው የማይዙ መሆኑን ሲሆን፣ ይህ ሁኔታ የሚወገዱ

ተሽከርካሪዎችን የማስወገዱ ተግባር በትክክል በመመሪያው መሠረት ስለመፈፀሙ ለማረጋገጥ አያስችልም፡፡

## ተሽከርካሪዎችን በማስወገድ የተገኘ ገቢ ለማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ መደረጉን በተመለከተ

135. የመንግስት ተሽከርካሪዎችን ከማስወገድ የሚገኝ ገቢ ለማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ መደረግ አለበት፡፡

136. በግብርና ሚኒስቴር የሚወገዱ ተሽከርካሪዎችን በማስወገድ የተገኘው ገቢ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፈሰስ መደረጉን የሚያስረዳ መረጃ ተጠይቆ ሊቀርብ አልቻለም፡፡

137. የመ/ቤቱ ግዥ፣ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክተር ሁኔታውን አስመልክቶ በቀረበላቸው የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት በመ/ቤቱ ከተወገዱ ተሽከርካሪዎች የተገኘው ገቢ በሙሉ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በወቅቱ ፈሰስ የተደረገ ቢሆንም ነባር ሰነዶች ከነበሩበት ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ተወስደው የተከማቹ በመሆኑ ወደ ኋላ ሂዶ እነዚህን ሰነዶች ፈልጎ ለመለየትና ለማቅረብ የማይቻል መሆኑን ገልፀዋል፡፡

138. መ/ቤቱ ተሽከርካሪን በማስወገድ የተገኘውን ገቢ በትክክል በወቅቱ ወደ ማእከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ ስለማድረጉ የሚያስረዳ መረጃ ሊቀርብ ባለመቻሉ ሁኔታውን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

## የተወገዱ ተሽከርካሪዎችን ከመዝገብ መሰረዝን በተመለከተ

139. ማንኛውም የመንግስት ተሽከርካሪ ከተወገደ በኃላ ከመዝገብ ሊሰረዝ እና ስለመወገዱ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚንስቴር ሪፖርት ሊደረግ ይገባል፡፡

140. በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የጐን ቁጥር 24138 ኒሳን ፒክአፕ፣ 25375 ኒሳን ፒክአፕ እና 30595 ፊያት ገልባጭ መኪናዎች በሽግግሩ ወቅት በ1983 ዓ.ም. መጥፋታቸው ስለአምቦ ነቀምት ፕሮጀክት ወቅታዊ ሁኔታ በቀረበው ሪፖርት ተገልጿል፡፡ በተጨማሪም የጐን ቁጥር 27726 ኒሳን ፒክአፕ መኪና በሥራ ላይ እንዳለ የኤርትራ ነፃነት ግንባር አሰብን በተቆጣጠረበት ወቅት እዛው መቅረቱ ከተሰበሰቡ እና ከተከለሱ መረጃዎች ለማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን፣ ባለሥልጣኑ በነዚህ ተሽከርካሪዎች ላይ አስተዳደራዊ ውሣኔ ሳይሰጥ ለ20

ዓመታት ያህል ተሸከርካሪዎቹን በንብረትነት መዝግቦ ይዞ ተገኝቷል። ስለጉዳዩ የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት መሠረት በሁለት ተቋማት የሚደራጅ እንደሆነና ከንብረት ክፍፍል በኋላ እንደተጠቀሱት አይነት ችግሮች እየተጣሩ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴርና ከባለስልጣን መ/ቤት ቦርድ ጋር በመመካከር ውሳኔ የሚሰጥበትን መንገድ እንደሚፈለግ ገልፀዋል፡፡

141. መጠይቅ ከተላከላቸው 33 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች በ4 መ/ቤቶች (12.12%) የተወገዱ ተሸከርካሪዎች ከመዝገብ እንዲሰረዙ አለመደረጉን ገልጸዋል፡፡

142. ስለጉዳዩ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ወደፊት በተለይ ለተሽከርካሪ በሚዘጋጀው መመሪያ ላይ መ/ቤቶች የተወገዱ ንብረቶችን የሚመለከት ሪፖርት ለኤጀንሲው ወይም እንደአስፈላጊነቱ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ማቅረብ እንዳለባቸው የሚያመለክት ድንጋጌ እንዲኖር ይደረጋል በማለት ገልጸዋል፡፡

143. መ/ቤቶች በስራቸው የሚገኙ ተሸከርካሪዎች በመመሪያው መሠረት ሲወገዱም ሆነ በተለያየ ምክንያት ሲጠፉ አሳማኝ መረጃዎችን በማቅረብ በወቅቱ አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ ጥረት እንደማያደርጉ፣ በዚህም ምክንያት የሌሉ ተሸከርካሪዎች በየዓመቱ በንብረትነት ተይዘው እንዲቆጠሩ ማድረጉ የተሳሳተ መረጃ እንዲያዝ ያደርጋል፡፡

## የመንግስት ተሸከርካሪዎችን ለማስተዳደር ተገቢው የሰው ኃይል የተመደበ መሆኑን በተመለከተ

144. የመንግስት መ/ቤቶች በስራቸው የሚገኙ ተሸከርካሪዎችን በብቃትና በቁጠባ ለማስተዳደር እንዲችሉ በተፈቀደላቸው የሥራ መደብ መሠረት የተሟላ የሰው ኃይል ሊኖራቸው ይገባል፡፡

145. በመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን፣ በማዕድን ሚኒስቴር፣ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር፣ በግብርና ሚኒስቴር፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና በውኃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የተሸከርካሪ ርክክብ፣ የስምሪትና፣ የነዳጅ ቁጥጥር እንዲሁም

የጥገና አገልግሎት በአግባቡና በተቀላጠፈ ሁኔታ ለማከናወን የሚያስችል የተሟላ የሰው ኃይል የሌላቸው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

146. ይህንንም በተመለከተ የሚመለከታቸው መ/ቤቶች የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን የድጋፍ ሰጪ ዳይሬክተር መካኒኮችን ለማሟላት በየጊዜው ጥረት እንደሚደረግ ሆኖም ግን ገበያ ላይ ለማግኘት እንደተቸገሩና ቢገኙም ቶሎ እንደሚለቁ፤ የማዕድን ሚኒስቴር ሚኒስትር በኦዲት ግኝቱ በተሰጠው አስተያየት መሠረት ወደፊት የሰው ኃይሉ እንደሚሟላ፤ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የደጋፊ የስራ ሂደቶች ማስተባበሪያ ዳይሬክተር በኦዲት ግኝቱ በተሰጠው አስተያየት መሠረት ወደፊት የሰው ኃይሉ እንደሚሟላ፤ የውኃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ የኦዲት ግኝቱ ትክክል መሆኑን፤ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ትልቅ ጋራዥ እንዲሆን እንደማይፈለግና ያለው የሰው ኃይል ለቀላል ጥገና የሚበቃ መሆኑን፤ የግብርና ሚኒስቴር ግዥና ፋይናንስ ንብረት አስተዳደር ዳይሬክተር የጋራዥ የአሠራር ሥርዓት ጥናት ተጠናቆ ወደ ትግበራ እየተገባ እንደሆነና የሰው ኃይሉም ከዚህ ጋር የሚታይ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

147. የመንግስት ተሽከርካሪዎች በብቃትና በቁጠባ ለመጠቀም እና ለመጠበቅ የሚያስችል የተሟላ የሰው ኃይል አለመመደቡ ተሽከርካሪዎችን በአግባቡ ለማስተዳደር የሚደረገው ጥረት ውጤታማ እንዳይሆን ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡

# ክፍል ሦስት

## መደምደሚያ

148. በመንግስት መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎችን መግዛት፣ ጥቅም ላይ ማዋል፣ መጠገን እና ተገቢውን እንክብካቤ ማድረግ እንዲሁም በብቃት አገልግሎት ሊሰጡ የማይችሉባቸው ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ማስወገድ በተሟላ የተሽከርካሪ ሥርዓት ውስጥ ዐብይ ሥፍራ የሚይዙ ተደጋጋፊ ተግባራት ናቸው፡፡ ለነዚህ ተያያዥ እና አስፈላጊ ተግባራት ተገቢው ትኩረት ሊሰጥ የሚገባ ቢሆንም በሀገራችን የመንግስት ተሽከርካሪዎችን በሚያስተዳድሩ መ/ቤቶች ለነዚህ ተያያዥ ተግባራት የሚሰጠው ትኩረት ሲታይ ተመጣጣኝ ሆኖ አይታይም፡፡

149. በመንግሥት ተሽከርካሪዎች አጠቃቀም እና አጠባበቅ ላይ ክፍተት የሚታይ በመሆኑ መንግሥት ይህን ሁኔታ በመገንዘብ ሁኔታውን ለማሻሻል የሚረዱ እርምጃዎችን ሲወስድ የቆየ ሲሆን፣ አገልገሎት የማይሰጡ እና ሊወገዱ የሚገባቸው ተሽከርካሪዎች ላይ ትኩረት በመስጠት በአወጋገዱ ላይ የሚታዩ ድክመቶችን ለማቃለል ይረዳሉ ያላቸውን መመሪያዎች በተለያየ ጊዜ አውጥቷል፡፡ ሆኖም የነዚህ መመሪያዎች ተግባራዊነት ሲታይ ግን ከፍተኛ ክፍተት ይታያል፡፡

150. የመንግሥት ተሽከርካሪዎች ካላቸው ከፍተኛ ዋጋ እና ለጥፋት ከመጋለጥ በሕርያቸው አንፃር የተለየ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው ቢሆንም የሚታየው አጠባበቅ እና አጠቃቀም ለአደጋ እና ለብክነት የመጋለጥ ሁኔታቸው ዝቅተኛ ለሆኑ ሌሎች ቋሚ ንብረቶች ከሚሰጠው ትኩረት ባልተለየ መልኩ እንደማንኛውም ቋሚ ንብረት የሚተዳደሩበት ሁኔታ ይታያል፡፡

151. በመሆኑም ለመንግስት ተሽከርካሪዎች ግዥ አፈፃፀም ሥርዓት ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ የሚፈፀም ቢሆንም ከፍተኛ ወጪ ወጥቶ የተገዙ ተሽከርካዎች ጥቅም ላይ በሚውሉበት ወቅት ሊደረግላቸው ለሚገቡ ጥበቃ፣ እንክብካቤ እና አወጋገድ ሥርዓቶች በተገቢው ሁኔታ ትኩረት ተሰጥቶ እንደማይፈጸሙ በኦዲቱ ወቅት ካገኘናቸው መረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

152. የመንግስት ተሽከርካሪዎች አጠባበቅ፣ አጠቃቀም እና አወጋገድ ሥርዐትን ለማሻሻል የመንግሥት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ እና ንብረቶቹን የሚገለገሉባቸው መ/ቤቶች ለጉዳዩ ተገቢውን ትኩረት ሰጥተው መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሀሳቦች

153. የመንግስት ተሽከርካሪንም ሆነ ንብረቶችን ለማስተዳደር የሚያስችል መመሪያዎችንና ደንቦችን ለማውጣት ስልጣን የተሰጠው አካል በተስጠው ሥልጣን መሠረት በሀገር አቀፍ ደረጃ የመንግስት ተሽከርካሪዎችን ለማስተዳደር ሀገርቱ አሁን ካለችበት ነባራዊ ሁኔታ አኳያ ሊያሰራ የሚችልና በጥናት ላይ የተመሠረተ መመሪያ ማዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ ይህም የመንግስት መ/ቤቶች ወጥ በሆነ መልኩ ተሽከርካሪዎቻቸውን ለማስተዳደር ስለሚረዳ የሚታየውን የተዘበራረቀ የተሽከርካሪዎቸ አስተዳደር ለማስተካከል ያስችላል፡፡

154. መ/ቤቶቹ የመንግስት ተሽከርካሪዎችን ለማስወገድ የሚረዱ ዝርዝር መረጃዎችን በተሟላ መልኩ በማጠናቀር ሊያዘጋጁ እና ለሚያስወግድው አካል በወቅቱ ማቅረብ ይኖርባቸዋል። ይህም ሊወገዱ የሚገባቸው ተሽከርካሪዎች ቀልጣፋ እና ተጠያቂነትን በሚያሳይ ሁኔታ እንዲወገዱ በማድረግ ለአላስፈላጊ ጥፋት እና ብክነት እንዳይዳረጉ የጎላ አስተዋጽኦ አለው።

155. የመንግስት መ/ቤቶች በስራቸው ያሉትን ተሽከርካሪዎች በየዓመቱ ቆጠራ እያደረጉ ተሽከርካሪዎቹ ያሉበትን ሁኔታ የሚያሳይ ልዩ ሪፖርት ለሚመለከተው አካል በወቅቱ ሊያቀርቡ ይገባል፡፡

156. የመንግስት መ/ቤቶች በስራቸው የሚገኙ ተሽከርካሪዎች የተጓዙበትን ኪሎ ሜትር ለመለካት የሚያስችል ጌጃቸው የሚሠራ መሆን አለመሆኑን በየጊዜው መከታተል ይኖርባቸዋል፡፡ የማይሠራ ሆኖ ሲገኝ ሊጠገን የሚችልበት ሁኔታ ሊመቻች፣ ሊጠገን ካልቻለ በአንድ ሊትር ነዳጅ ምን ያህል ኪ.ሜ መጓዝ እንደሚችሉ በአይነትና በሞዴል ተለይተው በጥናት ሊቀመጥ ይገባል፡፡ ይህም የነዳጅ አጠቃቀም በቁጠባ እና በብቃት እንዲከናወን ለማድረግ ያስችላል፡፡

157. የመንግስት መ/ቤቶች የሚያስተዳድሯቸው ተሽከርካሪዎች የነዳጅና ቅባት አጠቃቀም ላይ ወጥ በሆነ መልኩ ክትትል እና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህም ከቅባት እና ከነዳጅ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ የሚከሰተውን ከፍተኛ ብክነት በመቀነስ መንግስትን ከከፍተኛ ወጪ ለማዳን ያስችላል፡፡

158. የመንግስት መ/ቤቶች በኃላፊነት የሚያስተዳዱራቸውን ተሽከርካሪዎች እና መለዋወጫ እቃዎቻቸውን ከስርቆት እና ከብክነት ለመጠበቅ እና ለመከላከል አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ ሊወስዱ እና ተመሳሳይ ችግሮች እንዳይከሰቱ ቅድመ ጥንቃቄ በማድረግ የተከሰቱትን ችግሮች ለመቆጣጠር የሚያስችል የቁጥጥር ሥርዓት ሊዘረጉና ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

159. አገልግሎት የሚሰጡ የመንግስት ተሽከርካሪዎች አስፈላጊው የመድህን ዋስትና ሽፋን እንዲገባላቸው ሊደረግ እና ያረጁ በመሆናቸው እና በተለያዩ ምክንያቶች የመድን ዋስትና ሊያገኙ ያልቻሉ ተሽከርካሪዎች ሊወገዱ የሚችሉበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

160. የመንግስት መ/ቤቶች በስራቸው የሚያስተዳድራቸውን ተሽከርካሪዎች ከድንገተኛ የእሳት አደጋ ለመከላከል የሚረዳ የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሳሪያ (fire extinguisher) እንዲኖራቸው፣ እነዚህ መሳሪያዎችም አገልግሎት የሚሰጡ መሆኑን እና አለመሆኑን በተመለከተ በየጊዜው ክትትል ሊደረግ እና ስለአጠቃቀማቸውም ለአሽከርካሪዎች ስልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡ ይህም በድንገተኛ አደጋ ሊደርስ የሚችለውን ከፍተኛ ጥፋት በቀላሉ ለመከላከል ያስችላል፡፡

161. የመንግስት መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎቻቸው ከስርቆት፣ በኃላፊነት ያልተረከበ አካል እንዳያሽከረክር፣ ከተመደቡበት የመንግስት ዓላማና ሥራ ውጪ አገልግሎት እንዳይሰጡ ለመከላከል እና ለመቆጣጠር እንዲቻል በተሽከርካሪዎቻቸው በሁለቱ የጎን በሮቻቸው ላይ የመ/ቤታቸውን ዓርማ እንዳለጠፉ ሊደረግ ይገባል፡፡

162. የመንግስት መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎቻቸው በውጭ ጋራዥ እንዲጠገኑ በሚያደርጉበት ወቅት በቅድሚያ የውጭ የጥገና አገልግሎት የሚሰጠው ጋራዥ

ብቃት፣ ጥራት፣ ታማኝነትን ወ.ዘ.ተ… ለማረጋገጥ የሚያስችል የውጭ ጋራዥ የመምረጫ መስፈርት ሊኖራቸው ይገባል፡፡

163. የመንግስት መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎቻቸው ለጥገና ጋራዥ በሚገቡበት ውቅት በትክክል መበላሸታቸውን የሚፈትሽ፣ የሚያስፈልጋቸው መለዋወጫ፣ የሰው ኃይል እና የጥገና ጊዜ የሚወስን፣ ጥገና ተደርጎላቸው ሲወጡም በጥገና ወቅት የተፈቀዱላቸው መለዋወጫዎች በተሽከርካሪዎቹ ላይ ስለመገጠማቸው እና በተቀመጠላቸው የጥገና ፕሮግራም መሠረት ጥገናው መከናወኑ የሚያረጋግጥ ከጋራዥ ክፍሉ ወይም ከጥገናው ተግባር ገለልተኛ የሆነ ራሱን የቻለ የቴክኒክ ኢንስፔክተር ሊኖራቸው ይገባል፡፡

164. ለጥገና የሚገቡ የመንግስት ተሽከርካሪዎች የጉዳቱን አይነት እና ስፋት ግምት ውስጥ ያስገባ የጥገና የጊዜ ሰሌዳ ሊዘጋጅላቸው እና ተግባራዊ እንዲያደርጉት ሊደረግ ይገባል፡፡

165. የመንግስት መ/ቤቶች ሊወገዱ የተወሰነባቸውንና የማስወገድ ሂደት በመጠባበቅ ለሚገኙ ተሽከርካሪዎቻቸው ለቁጥጥር በሚያመች መልኩ ተበላሽተው በጥገና ከሚገኙና አገልግሎት ከሚሰጡ ተሽከርካሪዎች ለይተው ሊያስቀምጥዋቸው ይገባል፡፡

166. የመንግስት መ/ቤቶች እረጅም እድሜ ከማገልገላቸው የተነሳ በብቃትና በቁጠባ አገልግሎት የማይሰጡ ተሽከርካሪዎቻቸውን ለማስወገድ የሚረዳ በጥናት ላይ የተመሠረተና በአገር አቀፍ ደረጃ የተዘጋጀ የተሽከርካሪ ያገልግሎት ዘመን እንዲወሰን ሊደረግ ይግባል፡፡

167. በመንግስት ንብረት አወጋገድ መመሪያ መሠረት በመንግስት መ/ቤቶች ቢያንስ 3 አባላት ያሉት አስወጋጅ ኮሚቴ በበላይ ኃላፊ በመሰየም ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

168. የሚወገዱ የመንግስት ተሽከርካሪዎችን የሚያስወግድው አካል ሊወገዱ የሚገባቸውን ተሽከርካሪዎች ለማስወገድ የሚረዱ ዝርዝር መረጃዎችን ማለትም የተሽከርካሪ የታሪክ ማህደር እንደአግባብነቱ ቢያንስ ሊይዛቸው የሚገቡ የተሽከርካሪው ሞዴልና ሰሪው ፋብሪካ፣ የተሰራበት ሃገር፣ የተሰራበትና

የተገዛበት ዘመን፣ የተገዛበት ዋጋና የጉምሩክ ዲክለራሲዮን፣ የቻሲ ወይም ሴሪያል ቁጥር፣ የሞተር ቁጥርና የሰሌዳ ቁጥር ፣የነዳጅ አይነት፣ ለጥገና የወጣው ወጪ፣ አገልግሎት ያቋረጠበት ምክንያትና ጊዜው በተሟላ መልኩ መረጃ የሚያዝና የሚቀርብ ለመሆኑ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

169. አንድ የመንግስት ተሽከርካሪ በተለያየ ምክንያት ማለትም በከፍተኛ ጉዳት ምክንያት ሊጠገን የማይችል ከሆነ፣ የመለዋወጫ እቃ ከሌለ፣ ለማደስ የሚያስፈልገው ወጪ ከፍተኛ ከሆነ፣ ምርታማነቱ ዝቅተኛ ከሆነ፣ አጠቃላይ የጥገና ወጪው ከበዛ እና የአገልግሎት ጊዜው እረጅም ከሆነ በአጠቃላይ ከአገልግሎት ውጭ ሲሆኑ በየወቅቱ በመመሪያው መሠረት ሊወገድ ይገባል፡፡

170. የመንግስት ተሽከርካሪ ሲወገድ የተሻለውን የመሸጫ ዘዴ (በሃራጅ ወይም በጨረታ) መምረጥና ውሳኔው የበለጠ ዋጋ ከማግኘትና ሽያጩን ለማከናወን የሚኖረውን ፍጥነት ባገናዘበ ሁኔታ በመመሪያው መሠረት እንዲወገድ ማድረግ እና የተወገዱ ተሽከርካሪዎች መረጃ በአግባቡ ተጠናቅሮ የሚያዝ መሆኑን በተመለከተ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

171. የመንግሥት ተሽከርካሪን በማስወገድ የተገኘውን ገቢ መ/ቤቶች ወደ መንግስት ሳጥን ፈሰስ የሚያደርጉ ስለመሆኑ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

172. የመንግስት መ/ቤቶች በስራቸው የሚገኙ ተሽከርካሪዎች በመመሪያው መሰረት ሲወገዱም ሆነ በተለያዩ ምክንያቶች ሲጠፉ ወቅታዊ አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወስድ እና አሳማኝ ሆኖ ሲገኝም ከመዝገብ እንዲሰረዙ ሊደረግ ይገባል፡፡

173. የመንግስት መ/ቤቶች በስራቸው የሚገኙ ተሽከርካሪዎች በብቃትና በቁጠባ ለመጠቀምና ለማስተዳደር የሚያስችል በተፈቀደላቸው የሥራ መደቦች መሠረት በቂ የሰው ኃይል ያላቸው መሆኑን በተመለከተ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

174. በአጠቃላይ የመንግስት ተሽከርካሪዎች አጠባበቅ፣ አጠቃቀም እና አወጋገድ ሥርዓትን ለማሻሻል ንብረቶቹን የሚገለገሉባቸው መ/ቤቶች ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተው መንቀሳቀስ የሚጠበቅባቸው ቢሆንም የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የዚህን ቋሚ ንብረት ለብክነት እና ለጥፋት በቀላሉ

የመጋለጥ ልዩ ሁኔታ በመገንዘብ በመረጃዎች አያያዝ፣ በአጠቃቀም፣ በጥገና፣ ብሎም በአወጋገድ ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን በመለየት እንደመርሀ የሚያገለግል መመሪያ ከማዘጋጀት ጀምሮ በየጊዜው በተግባራዊነቱ ላይ የሚታዩ ችግሮችን የቅርብ ክትትል በማድረግ ለመ/ቤቶቹም ሆነ ለሚመለከከተው የመንግስት አካል በማቅረብ የማሻሻያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ እና በዚህ ረገድ የሚታዩ የአሠራር ድክመቶች እንዲሻሻሉ ጥረት ሊያደርግ ይገባል፡፡

በመጨረሻም ኤጀንሲው እንዲሁም በናሙና ተመርጠው የታዩ የፌዴራል መ/ቤቶች እና ሠራተኞች ላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

# አባሪዎች

አባሪ 1

## <u>የኦዲት መስፈርት መመዘኛዎች</u>

**የመንግስት ተሽከርካሪዎችን ስምሪት በብቃት እና በቁጠባ አገልግሎት እየሰጡ መሆናቸውን ለመቆጣጠር እና ለመከታተል የሚያስችል ሥርዓት መኖሩን እና ተግባራዊ መደረጉን ማጋገጥ፤**

1. በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥ የሆነና በጥናት ላይ የተመሰረተ የመንግስት ተሽከርካሪዎች አጠቃቀም መመሪያ ሊዘጋጅ እና ለመንግስት መ/ቤቶች እንዲሠራጭ ሊደረግ ይገባል፡፡
2. ይህ በሀገር አቀፍ ደረጃ የወጣው የመንግሥት ተሽከርካሪዎች አጠቃቀም መመሪያ በየጊዜው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እንዲሻሻል ሊደረግ ይገባል፡፡
3. የመንግስት መ/ቤቶች በኃላፊነታቸው ሥር የሚገኙ ተሽከርካሪዎች በሚመለከት አስፈላጊው ዝርዝር መረጃ ሊይዝ ይገባል (ለምሳሌ፡ እንደት ወደ መ/ቤቱ እንደመጡ፣ የተጓሁትን ኪሎሜትር፣ የተጠቀሙትን ነዳጅ፣ቅባት እና ለሎችም ተዛማጅ ቁሳቁሶች፣ የተደረገላቸውን ጥገናና የወጣውን ወጪ) መረጃዎቹም ኮምፒተራይዝድ በሆነ መልኩ ሊያዙ ይገባል፡፡
4. የመንግስት መ/ቤቶች በሥራቸው የሚገኙ ተሽከርካሪዎችን ስምሪት በአግባቡ ለመከታተል እና ለመቆጣጠር የሚያስችላቸው ሥርዓት ሊዘረጉ እና ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡
5. የመንግስት መ/ቤቶች የሚያስተዳድሯቸውን የመንግስት ተሽከርካሪዎች አጠቃላይ ሁኔታ የሚገልጽ ልዩ ሪፖርት በየዓመቱ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚንስቴር ማቅረብ አለባቸው፡፡
6. የመንግስት መ/ቤቶች የተሽከርካሪ የነዳጅና የቅባት አጠቃቀም መመርያ ሊኖራቸው ይገባል፡፡
7. የመንግስት ተሽከርካሪዎች መንቀሳቀስ ያለባቸው ህጋዊ የሆነ መንጃ ፍቃድ ባለው እና በመመሪያው መሠረት በተፈቀደለት ሰው ብቻ ሊሆን ይገባል፡፡

8. የመንግስት ተሽከርካሪዎች የሚያንቀሳቅስ ማንኛውም የተፈቀደለት ሰው በቅድሚያ ስለተሽከርካሪ ደህንነት እና አጠባበቅ ሊያውቃቸው የሚገቡ መሠረታዊ ነጥቦችን ማወቁ ሊረጋገጥ እና የግንዛቤ ችግር ካለ ግንዛቤ እንዲኖረው ሊደረግ ይገባል፡፡

9. የመንግስት መ/ቤቶች ለሚያስተዳድሯቸው ተሽከርካሪዎች የመድህን ዋስትና (ኢንሹራንስ) እንዲኖራቸው ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

10. የመንግስት መ/ቤቶች ለሚያስተዳድሯቸው እና በኃላፊነት የተረከቡአቸውን ተሽከርካሪዎች ለሌላ ላልተፈቀደለት አካል አሳልፎ መስጠት የለባቸውም፡፡

11. ኤጀንሲው በማናቸውም የፌዴራል መንግስት መ/ቤት ሥር ያልሆኑ የፌዴራል መንግስት ተሽከርካሪዎች በመንግስት ንብረትነት ይይዛል ፤ ያስተዳድራል፤ ተገቢ ሆኖ ሲገኝ እንዲወገዱ ማድረግ አለበት፡፡

12. የመንግስት መ/ቤቶች በሚያስተዳድሯቸው የመንግስት ተሽከርካሪዎች በሁለቱም የጎን በሮቻቸው ላይ የመ/ቤቱ ዓርማ ማድረግ አለባቸው፡፡

13. የመንግስት ተሽከርካሪ የመጠበቅ ኃላፊነት የሚወድቀው ተሽከርካሪውን በኃላፊነት በተረከበው አካል መሆን አለበት፡፡

14. የመንግስት ተሽከርካሪዎች ከተመደቡበት የመንግስት ዓላማ እና ሥራ ውጪ አገልግሎት መስጠት የለባቸውም ፡፡

15. ማንኛውም የመንግስት ተሽከርካሪ የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሳሪያ (fire extinguisher) ሊኖረው ይገባል፡፡

16. የመንግስት ተሽከርካሪዎች በዓይነትና በሞዴል ተለይተው በአንድ ሊትር ነዳጅ ስንት ኪሎሜትር መጓዝ እንደምችሉ በጥናት ሊረጋገጥና የተሽከርካሪዎችም ኪሎሜትር መቆጣጠሪያ ጌጅ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

**የመንግስት ተሽከርካሪዎችን ጥገና በብቃት እና በቁጠባ መከናወኑን ለመቆጣጠር እና ለመከታተል የሚያስችል ሥርዓት መዘጋጀቱን እና ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ**

17. የመንግስት ተሽከርካሪዎች የጥገና መመሪያ ሊዘጋጅ እና ለሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶቸ ሁሉ እንዲደርስ ሊደረግ ይገባል፡፡

18. የመንግስት መ/ቤቶች የተሽከርካሪ የውጭ ማስጠገኛ ጋራዥ የመምረጫ መስፈርት ሊኖራቸው እና ተግባራዊ ሊያደርጉት ይገባል፡፡

19. አዲስ የተገዙ የመንግስት ተሽከርካሪዎች ከአስመጪ ኩባንያ ጋር በሚደረገው ስምምነት በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ሰርቪስ ማስደረግ አለባቸው፡፡

20. የመንግስት ተሽከርካሪዎች ለጥገና ጋራዥ ከመግባታቸው በፊት የደረሰባቸው ብልሽት በባለሙያ ሊረጋገጥ እና በሚመለከተው የሥራ ኃላፊ ሊጸድቅ ይገባል፡፡

21. የመንግስት ተሽከርካሪ ለጥገና ጋራዥ ሲገባ እንደብልሽቱ አይነት በተቀመጠለት የጥገና የጊዜ ገደብ መስረት ተጠግኖ አገልግሎት ላይ መዋል አለበት ካልሆነም በተቀመጠለት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ተጠግኖ ያልወጣበት በቂ ምክንያት ሊገለጽና የሚመለከተው የሥራ ኃላፊ ሊያረጋግጠው ይገባል፡፡

22. የመንግስት ተሽከርካሪዎች ጥገና ተደርጎላቸው ጥገናውን ካደረገው አካል ርክክብ ከመደረጉ በፊት በባለሞያ(technical inspector) ተገቢው ጥገና ስለመከናወኑ እንዲረጋገጥ ሊደረግ ይገባል፡፡

23. የመንግስት ተሽከርካሪዎች አገልግሎት የሚሰጡ፣ ለጊዜው ተበላሽተው ጥገና በመጠባበቅ ላይ ያሉ እና ፈጽሞ አገልግሎት መስጠት የማይችሉ ተብለው ተለይተው መቀመጥ አለባቸው፡፡

24. ፈጽሞ አገልግሎት መስጠት የማይችሉ ሊወገዱ የሚገባቸው የመንግስት ተሽከርካሪ መረጃዎች በአግባቡ ተጠናቅሮ እና ተያይዞ የሚወገዱ ንብረቶችን ለሚያስወግድ አካል ሊተላለፍ ይገባል፡፡

## የመንግስት ተሽከርካሪዎች ማገልገል የሚገባቸውን ጊዜ ያህል እያገለገሉ ስለመሆኑ ማጣራት

25. በሀገር ደረጃ አንድ የመንግስት ተሽከርካሪ ምን ያህል ዘመን ሊያገለግል እንደሚችል በጥናት ሊወሰን ይገባ፡፡

26. በጥናት የተወሰነውን የአገልግሎት ጊዜአቸውን ሳይጨርሱ ከአገልግሎት ውጪ ለሚሆኑ ተሽከርካሪዎች ተገቢ እና የተረጋገጠ ምክንያት ሊቀመጥ ይገባል፡፡

**መወገድ የሚገባቸውን የመንግስት ተሽከርካሪዎች ለማስወገድ መንግስት ያወጣው መመሪያ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑ እና የማስወገዱ ተግባር በቁጠባ እና በብቃትእየተከናወነ መሆኑን መገምገም፡፡**

27. በአወጋገድ መመሪያው መሰረት በመንግስት መ/ቤቶች ቢያንስ ሶስት አባላት ያለው የተሽከርካሪ አስወጋጅ ኮሚቴ በበላይ ሀላፊ አቅራቢነት  መሰየም አለበት፡፡

28. የሚወገዱ የመንግስት ተሽከርካሪዎችን ለሚያስወግድ አካል ሊወገዱ የሚገባቸው ተሽከርካሪዎችን ለማስወገድ  የሚያስፈልጉ ዝርዝር ማስረጃዎችን  የያዘ  እና የተጠናቀረ መረጃ ሊቀርብ ይገባል፡፡

29. አንድ የመንግስት ተሽከርካሪ ከሚሰጠው አገልግሎት በላይ ወጪ የሚያስወጣ ወይም አገልግሎት መስጠት የማይችል ከሆነ መወገድ አለበት፡፡

30. በጨረታ፣ በሀራጅ እና በዝውውር የሚወገዱ የመንግስት ተሽከርካሪዎች አወጋገድ በአወጋገድ መመሪያው መሰረት ሊፈጸም ይገባል፡፡

31. የመንግስት ተሽከርካሪ ሲወገድ የወቅቱን የገበያ ሁኔታ(የጨረታው ውጤት የሰጠው ዋጋ) ያገናዘበ መሆን ይገባል፡፡

32. የመንግስት ተሽከርካሪዎች በማስወገድ የተገኘ ገቢ ለማዕከላዊ ግምጃ ቤት ገቢ መደረግ አለበት፡፡

33. ተሽከርካሪ ከአንድ የመንግስት  መ/ቤት ወደ ሌላ መንግስት መ/ቤት  ሲዘዋወር የማዘዋወርያ ዋጋው ከመዘዋወርያ ዋጋ ግምት ጋር እኩል መሆን  አለበት፡፡

34. ማንኛውም ተሽከርካሪ ከተወገደ በኃላ ከመዝገብ ሊሰረዝ እና ስለመወገዱ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚንስቴር ሪፖርት ሊደረግ ይገባል፡፡